ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 112 ታኅሣሥ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# በከሠም ግድብ

## በዓመት ከ13 ሺ ኩንታል በላይ ፍራፍሬ ይመረታል

**ሪስወርቅ ሙሉጌታ**

አፋር፡- በከሠም ግድብ በ72 ሄክታር መሬት በዓመት ከ13 ሺ ኩንታል በላይ ፍራፍሬ እየተመረተ ይገኛል።

በከሠም ስኳር ፋብሪካ የእርሻ ኦፕሬሽን ዘርፍ ሥራ አስኪያጅ አቶ ሠለሞን ጋኖሬ የፍራፍሬ ልማቱን አስመልክተው እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ወቅት በፋብሪካው እየለማ የሚገኘው ብርቱካን፣ መንደሪንና ማንጎ ሲሆን በዚህም ሁለት መቶ ለሚደርሱ ዜጎች በጊዜያዊነት፤ በኮንትራትና በቋሚነት የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል። የፍራፍሬ ምርቶቹንም የአካባቢው ነዋሪዎች በማኅበር ተደራጅተው በተመጣጣኝ ዋጋ በመቀበል እያከፋፈሉ ይገኛል። በተመሳሳይ ፋብሪካው ከኢትፍሩት ጋር ውል በመግባት ምርቱን እያስረከበ ይገኛል።

በከሠም ግድብ በዓመት... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በክልሉ የየብስ ትራንስፖርትን ሙሉ ለሙሉ ለማስጀመር እየተሠራ ነው

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ከተለያየ አቅጣጫ ወደ ክልሉ የሚገቡ የየብስ ትራንስፖርት እንቅስቃሴዎችን ሙሉ ለሙሉ ለማስጀመር እየተሠራ መሆኑን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስታወቀ፡፡

የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) የክልሉን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክተው ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ ከየብስ ትራንስፖርት አንጻር የገጠመውን ችግር ሙሉ ለሙሉ ለመቅረፍ እየተሠራ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ በተለይ በመጪው የገናና የጥምቀት በዓላት መዳረሻ ድረስ የፀጥታ ኃይሉ ከፌዴራልና ከክልል የፀጥታ አካላት ጋር ጥምረት በመፍጠር ሠላም እንዲሰፍን፣ ትራንስፖርት እንዳይቆራረጥ፣ እንግዶች እንዳይንገላቱ፣ ከተለያየ አቅጣጫ ወደ ክልሉ የሚገቡ የየብስ ትራንስፖርት

በክልሉ የየብስ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









## የካፒታል ገበያ- ኢኮኖሚን የማሳደግ አንዱ ስልት

ገጽ 6




# በኢትዮጵያ በየዓመቱ 19 ሚሊዮን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ይባክናል

•አንድ ሺህ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ ማኅበራት ከገበያ ወጥተዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በየዓመቱ ከሚመረተው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት 19 ሚሊዮኑ እንደሚባክን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ አንድ ሺህ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ ማኅበራት ከገበያ ውጭ መሆናቸውም ተጠቁሟል፡፡

በቆዳና ሌጦ ምርትና የግብይት ደረጃ፣ ተግዳሮቶችን እና ተስፋዎች ላይ ያተኮረ ዓውደ ጥናት በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አዘጋጅነት ሲካሄድ በመድረኩ ላይ የተገኙት በግብርና ሚኒስቴር የሥጋ፣ ቆዳና ሌጦ ዘርፍ ዴስክ ኃላፊ አስመላሽ በርሄ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በየዓመቱ ከዳልጋ ከብቶች፣ ከፍየልና ከበግ

በኢትዮጵያ በየዓመቱ 19 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



# በሀገሪቱ ከሚታረሰው መሬት በምርጥ ዘር የተሸፈነው ከ20 በመቶ በታች ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ከሚታረሰው መሬት እስካሁን በምርጥ ዘር የተሸፈነው ከ20 በመቶ በታች መሆኑን የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስትቲዩት አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜትና ዘር ምርምር ዳይሬክተር ካርታ ካስኬ(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በሀገሪቱ ከሚታረሰው አጠቃላይ መሬት በምርጥ ዘር እስካሁን የተሸፈነው ከ20 በሙቶ የዘለለ አይደለም።

የቀረው መሬት ዘር የተሸፈነው በተለመደው መንገድ ነው ያሉት ዶክተር ካርታ፤ ጥራቱን የጠበቀ ምርጥ ዘር ከመዝራት ረገድ ያለው ግንዛቤም አነስተኛ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ኢንስቲትዩቱ ከተቋቋመ አንስቶ እስከ አሁን በሀገሪቱ ከአንድ ሺህ 400 በላይ የተሻሻሉ ዝርያዎች ቢኖሩም በአርሶ አደሩ እጅ ገብተው አገልግሎት እየሰጡ ያሉት ጥራት ያላቸው ዘር ቁጥር ውስን ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ካርታ ገለጻ፤ የአርሶ አደሩ የግንዛቤ ችግር፤ የመረጃ እጥረት፣ የሎጅስቲክ ችግር፣ አልፎ አልፎ የተወሰኑ የምርጥ ዘር ዝርያዎች ላይ ብቻ ማተኮር እንዲሁም የምርጥ ዘር ግብዓት እጥረት መከሰቱ በሃገሪቱ የምርጥ ዘር እንዳይስፋፋ አድርገውታል።

ዶክተር ካርታ አክለውም፤ በዘር ሥርዓቱ ላይ ያሉ ባለድርሻ አካላት መዋቅራዊ አሠራር ላይ ክፍተት መኖር ተጠቃሽ እንደሆነ ተናግረዋል።

ችግሩን ለመቅረፍና የአርሶ አደሩን ምርጥ ዘር የመጠቀም ግንዛቤ ለማሳደግ ሰፋፊ ሰርቶ ማሳያዎች እየተሠሩ እንደሆነም ነው ዶክተር ካርታ የገለጹት።

ሠርቶ ማሳያዎቹ በተሠራባቸው አካባቢዎችም የገበሬዎች ምርጥ ዘር የመጠቀም ፍላጎት ጨምሯል ያሉት ዶክተር ካርታ፤ የአርሶ አደሩን የምርጥ ዘር አጠቃቀም ለማሳደግና ምርጥ ዘር ተደራሽነት ለማስፋት የአሠራር ማሻሻያዎች ተደርጓል ብለዋል።

በዘር ሥርዓቱ ውስጥ የሚሳተፈው በተለይ ዘር አባዦች ፍላጎቶቻቸውንና እቅዳቸውን ቀድመው የሚያሳውቁበት ሥርዓት ተዘርግቷል።

የተሻሻሉ ዝርያዎች መጠቀሙ የአየር ፀባይንና ከአፈር ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቋቋም እንዲሁም የሌሎች ግብዓቶች አጠቃቀም ለማዘመን እንደሚያግዝ ዶክተር ካርታ መክረዋል።

እንደ ዶክተር ካርታ ገለጻ፤ ጥራቱ የጠበቀ ዘር በየዓመቱ በአማካይ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የሚዘጋጅ ቢሆንም ጥራቱን የጠበቀ ዘር የሚጠቀመው አርሶ አደር አጠቃላይ በግብርና ከተሰማራው አርሶ አደር አንጻር ሲታይ ትንሽ ነው።

ዶክተር ካርታ፤ በምርጥ ዘር አቅርቦት ዙሪያ ያሉ ውስንነቶችን ለመቀነስ ዘር አባዦች የሚፈልጉትን ያክል በአጭር ጊዜ እንዲያሳውቁ እንዲሁም አርሶ አደሩ ስለአዳዲስ ዝርያዎች መረጃ በመውሰድ ግንዛቤ ማዳበር እንዳለበት አስገንዘበዋል።

የግል ባለሃብቶችና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ምርጥ ዘር ሠርቶ በማሳየትና የማስፋፋት ሥራዎችን ከምርምር ኢንስቲትዩቱ ጋር በጋራ መሥራት እንዳለባቸውም ዶክተር ካርታ አሳስበዋል።

# የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የውጭ ግንኙነትን እንዴት መደገፍ ይችላሉ ?

**ተስፋ ፈሩ**

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅሞች በማስጠበቅ ረገድ በዘላቂነት መሥራት የሚችሉበትን መደላድል ለመፍጠር ያለመ የምክክር መድረክ በውጭ ጉዳይ ኢንስቱቲዩት እና በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን አዘጋጅነት በቅርቡ መካሄዱ ይታወሳል።

በኢትዮጵያ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ቁጥር ከጎረቤት ሀገራት ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ መሆኑን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን መረጃ ያመለክታል፡፡ ድርጅቶቹ በሌሎች ሀገራት ከሚገኙ ተመሳሳይ አደረጃጀት ካላቸው አቻ መንግሥታዊ ያልሆኑ አደረጃጀቶች አንጻር የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በመደገፍ ረገድም ተጠቃሽ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አይስተዋልም፡፡

ለመሆኑ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ የምታደርገውን ጥረት እንዴት ማገዝ ይችላሉ ?

የፖለቲካ ሳይንስ ምሑሩ የቻለ ደጉ (ዶ/ር) የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ሀገሪቱ በምታሠማራቻው ዲፕሎማቶች ብቻ እንደማይተገበር ይናገራሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች መኖራቸውን ጠቁመው፣ እንዳለመታደል ሆኖ ግን እነዚህ ድርጅቶች የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በማስተዋወቅ ሥራ ላይ እንደማይሳተፉ ይገልጻሉ፡፡

እንደ የቻለ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ከአውሮፓና ከአሜሪካ የሚመጡ አምባሳደሮችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካገኙ በኋላ ሰፋ ያለውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር ነው፡፡ ሀገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር የሚኖራትን የወደፊት ግንኙነት የሚቀርጹትና ዕቅድ የሚያወጡት ከነሱ በሚያገኙት የተለያየ መረጃና ግብዓት ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ከምዕራባውያን መንግሥታት ጋር ያላቸውን ግንኙነት መረዳት አለበት ያሉት የፖለቲካ ሳይንስ ምሑሩ፤ የሀገር ውስጥንም ሆነ የውጭ ፖሊሲዎቹን በማስተግበር ሂደት ውስጥ አንዳንድ ፍላጎቶቹን ለምዕራባውያን ሀገራት በማድረስ ረገድ ብልሃት በተሞላበት መንገድ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን እገዛ ለማግኘት መንቀሳቀስ መቻል አለበት ሲሉ ይመክራሉ፡፡

ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም በበኩላቸው የሚሠሯቸው የዴሞክራሲ እና የሰብዓዊ መብት ሥራዎች ከውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የተነጠሉ አለመሆናቸውን መረዳት እንዳለባቸው አመላክተው፤ "የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና የዴሞክራሲ እና የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰብዓዊ መብት ጥሰትን የሚከላከሉትና ዴሞክራሲን የሚያሰፍኑት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን ዘንግተው መሆን የለበትም" ብለዋል፡፡

አያይዘውም ሌሎች ጉዳዮችን እንደሚያቀነቅኑትና የማግባባት ሥራ እንደሚሠሩት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲንም ዴሞክራሲን እና የሰብዓዊ መብትን ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ማቀንቀንና ማስተዋወቅ መቻል እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡

የፖለቲካ ሳይንስ ምሑሩ አስተያየታቸውን ሲያጠቃልሉ እንደተናገሩት፤ የሀገሪቱን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሚያወጣውና የሚያስፈጽመው አካል የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እንዲተገበር አስተዋፅዖ የሚያደርጉት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በጋራ መሥራት አለበት፡፡ ይህን ማድረግ የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ያገኛል፡፡ በሌላ በኩል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚያነሷቸውን ሀሳቦች ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎች እንዲወጡና እንዲተገበሩ እድል ይሰጣል፡፡

የአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ዳይሬክተር እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ትነበብ ብርሃኔ በበኩላቸው፤ የልማት አጋሮች እንደመሆናችን መጠን ሥራችን ከተለያዩ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ስለሚያያዝ ግንኙነታችን በአብዛኛው ከውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጋር የተገናኘ ነው ይላሉ፡፡

የልማት አጋርነት የሚመጣው ሀገራት በውጭ ግንኙነት ፖሊሲያቸው ላይ ተመሥርተው ከሚያደርጓቸው ግንኙነቶች ጋር ተያይዞ መሆኑን ጠቁመው፤ ለጋሾች ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡበት ዋና ምክንያት በውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ውስጥ ከሚኖራቸው አጀንዳ ጋር እንደሚያያዝ ይገልጻሉ፡፡

"እኛ ሀገራችን እንድትለማና የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ነው የምንፈልገው ይህን ግባችንን ለማሳካት እስካገዘን ድረስ በዓለም አቀፍ መድረኮች ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ መሥራትን በመልካም መንፈስ የምንቀበለው ነው" ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቷ፤ መንግሥት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በፐብሊክ ዲፕሎማሲ ላይ ትልቅ ሚና እንዳላቸው ተረድቶና ያንን አክብሮ ከተለያዩ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በምናደርገው ግንኙነት የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እንድናስተዋውቅና በጎ ተፅዕኖ እንድንፈጥር ከእኛ ጋር ለመሥራት መነሳቱ ትልቅ እርምጃ ነው ብለዋል፡፡

አክለውም፤ መጀመሪያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አቅጣጫዎች በደምብ መረዳትና መተንተን ይኖርብናል፡፡ ከዚያ በኋላ ከተለያዩ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በሚኖሩን ግንኙነቶች አጀንዳ ሆኖ መነሳቱ ስለማይቀር ያን ጊዜ ሀገራችንን ወክለን የሚያስፈልገውን ማብራሪያ ለሚያስፈልገው አካል የመስጠት ሥራ መሥራት እንችላለን ብለዋል፡፡

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን መረጃ እንደሚያመለክተው በተሻሻለው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት፣ ከሚያዚያ 2011 ዓ.ም ጀምሮ በተካሄደው አዲስ ምዝገባ በቀድሞ አዋጅ ቁጥር 621/2001 ተመዝግበው ከነበሩ መካከል 1805 ድርጅቶች ዳግም የተመዘገቡ ሲሆን ከ1300 በላይ ተጨማሪ አዳዲስ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ተመዝግበዋል፡፡ በድምሩ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ 2005 የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በትምህርት፣ በጤና፣ በምግብ ዋስትና፣ በአካባቢ ጥበቃ ወዘተ. መንግሥትን በማገዝ ከፍተኛ ለውጦች በማስመዝገብ ላይ እንደሚገኙ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ መረጃ ያሳያል፡፡ ድርጅቶቹ በሌሎች በርካታ መስኮች እያደረጉ ያለውን ከፍተኛ አስተዋፅዖ የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በማስተዋወቅ ሥራም የሚደግሙት ከሆነ፣ ኢትዮጵያ በተለይም ከምዕራባውያን ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ይበልጥ እንዲጠናከር የሚያግዝ ይሆናል፡፡

# 17 ሚሊዮን ሰዎች የተተከሉ ችግኞችን ተንከባክበዋል

## - አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ እንክብካቤ ተደርጓል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ አምስት ወራት 17 ሚሊዮን ሰዎች በአረንጓዴ ዐሻራ የተተከሉ ችግኞች መንከባከባቸውን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ። በዚህም አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የተተከሉ ችግኞች እንክብካቤ ተደርጎላቸዋል።

በኢትዮጵያ ደን ልማት የአረንጓዴ ዐሻራና ሰው ሠራሽ ደን መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አበሩ ጠና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በበጀት ዓመቱ በአምስት ወራት 17 ሚሊዮን ዜጎች የተተከሉ ችግኞችን ተንከባክበዋል።

በ2015/16 በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር የተተከለው ችግኝ የጽድቀት መጠን በአጠቃላይ 81 ነጥብ ሁለት በመቶ መሆኑን አቶ አበሩ አመላክተዋል።

የችግኞቹን የጽድቀት መጠን ለመለየት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመሆን የመስክ ምልከታ ተደርጓል ያሉት አቶ አበሩ፤ ሠላም በሌለባቸው ክልሎችም ጭምር ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ እንደተቻለ ጠቁመዋል።

የአምስት ዓመቱን አጠቃላይ የጽድቀት መጠን ለመለየት በገለልተኛ አካል ጥናት እየተካሄደ እንደሆነም ነው አቶ አበሩ የተናገሩት።

እንደ አቶ አበሩ ገለጻ፤ እንክብካቤው የ2015/16 ብቻ ሳይሆን በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር እስካሁን የተተከሉ ችግኞችን የሚያካትት ነው። ማኅበረሰቡ ችግኝ ለመንከባከብ ያለው ግንዛቤ እንዲጨምር በባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍና በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች ግንዛቤ ሲደረግ ቆይቷል ብለዋል።

አቶ አበሩ አክለውም፤ የተተከሉ ችግኞች ከመንከባከብ ረገድ የመንግሥትና የወል ቦታዎች ላይ ክፍተቶች ነበር ያሉ ሲሆን፤ ክፍተቱን ለመሙላት ሲሠራ መቆየቱን አስታውቀውል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር ሳይንሳዊ መንገድ በተከተለ መልኩ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር የሚሠራ በመሆኑ በየዘርፉ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን አቶ አበሩ ጠቁመዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራው እንደተቋም የተጎዱ መሬቶችን ለመጠገን ነው ያሉት አቶ አበሩ፤ ሀገሪቱም በተለያዩ መድረኮች ላይ በ2030፤ 22 ሚሊዮን ሄክታር የተጎዱ መሬቶችን ለመጠገን ቃል ገብታ እየሠራች እንደምትገኝ አስታውሰዋል።

አቶ አበሩ አክለውም፤ ኢትዮጵያ ለዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ለምታበረክተው አስተዋፅዖ ተጠቃሚ ለማድረግ በተለይም በአረንጓዴ ዐሻራው ለሚሠሩ ፕሮጀክቶች የገንዘብ ፈንድ እንዲለቁና በየጊዜው ድጋፍ እንዲያደርጉ እየተደረገ ነው። ሀገሪቷ ደንን በመንከባከብና በመጠበቅ ከካርበን ሽያጭ ገቢ እንድታገኝ እየተሠራ ነው።

አቶ አበሩ፤ ለጎረቤት ሀገራት ችግኞች መሰጠቱን ጠቁመው፤ በሚቀጥለው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብርም ሀገራቱ በጠየቁት መሠረት ችግኞችን ለመስጠት ዝግጅት እተደረገ ነው።

በ2016/17 ክልሎች የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር ስምንት ነጥብ ዘጠኝ ቢሊዮን ችግኝ ለማዘጋጀት እቅዳቸውን አስገብተዋል ብለዋል።

እንደ አቶ አበሩ ገለጻ፤ ደን ላይ ኢንቨስት የሚያደርጉ ባለሀብቶች ፍላጎት እየጨመረ ነው። በኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ ኢኒሼቲቭ ብዙ ሀገራት ልምድ በመውሰድ ወደ ትግበራ እየገቡ መሆኑንም ገልጸዋል።

ዜና



ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ለገሠ

# የባሕር በር የንግድ ሚዛንን ስማስጠበቅና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ስመሳብ ጉልህ ሚና ይጫወታል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የባሕር በር ከሌሎች ሀገራት ጋር ያለንን የንግድ እንቅስቃሴ በማሳለጥ የንግድ ሚዛንን ለማስጠበቅና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ጉልህ ሚና እንደሚጫወት በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህር ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ለገሠ ገለጹ፡፡

ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ለገሠ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዓለም ላይ ከሚደረጉ የንግድ ግንኙነቶች 71 በመቶው በውሃ ላይ የሚደረጉ ናቸው። የባሕር በር ከሌሎች ሀገራት ጋር ያለንን የንግድ እንቅስቃሴ በማሳለጥ የንግድ ሚዛንን ለማስጠበቅና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ጉልህ ሚና ይጫወታል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ከአጠቃላይ የዓለም ሕዝብ አንድ ነጥብ 57 በመቶውን ይሸፍናል ያሉት ምሑሩ፤ ይህ ማለት ከእያንዳንዱ 200 የዓለም ሕዝብ ሦስቱ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ይህም ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በርካታ የሕዝብ ብዛት ኖሯት የባሕር በር የሌላት ሀገር ያደርጋታል ብለዋል፡፡

በዓለም ላይ ከሚደረጉ የንግድ ግንኙነቶች 71 በመቶው በውሃ ላይ የሚደረጉ ናቸው ያሉት ምሑሩ፤ ለዚህ ዋነኛ ምክንያቱ በሌሎች የትራንስፖርት አማራጮች የሚደረገው ንግድ ግንኙነት ውድ መሆን ነው ብለዋል፡፡

አውሮፕላንን በማሳያነት ብንወስድ ከባሕር ትራንስፖርት አንጻር ከ12 እስከ 16 እጥፍ የዋጋ ጭማሪ እንዳለው ጠቅሰው፤ የሚበላሹና ቶሎ መድረስ ካለባቸው ነገሮች ውጪ በአየር ትራንስፖርት ማጓጓዝ አዋጭ አይደለም ሲሉም ተናግረዋል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በ2014 ይፋ ባደረገው ጥናት አንድ ወደብ የሌላት ሀገር ያመረተችውን ምርት ወደ ውጪ ስትልክ በአማካይ በአንድ ኮንቴነር እስከ 3ሺህ204 ዶላር እንደምታወጣ የሚያመላክት መሆኑን ጠቅሰው፤ የባሕር በር ያላቸው ሀገሮች የሚያወጡት ደግሞ አንድ ሺህ 268 ዶላር ብቻ ነው ሲሉም ጠቅሰዋል።

ምርት የሚያስገቡ የባሕር በር የሌላቸው ሀገራትም ለአንድ ኮንቴነር 3 ሺህ 884 ዶላር እንደሚያወጡ ጠቁመው፤ የባሕር በር ያላቸው ሀገሮች ደግሞ አንድ ሺህ 443 ዶላር ያወጣሉ። የትራንስፖርት ወጪ እንዲሁም የወደብ ኪራይ እቃው ዋጋ ላይ ተጨምሮ ስለሚሸጥ የዋጋ ንረትን በማባባስ በኩል ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ሲሉም ጠቁመዋል፡፡

ይህም የባሕር በር የሌላቸው አገሮች ተወዳዳሪነታቸው ላይ ትልቅ እንቅፋት በመፍጠር የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንት እንዲቀንስ ያደርጋል ያሉት ባለሙያው፤ የንግድ ሚዛንን በማዛባት በኩልም ከፍተኛ ጫና ያሳድራል ብለዋል፡፡


በጥቅሉ የባሕር በር ባለመኖሩ ምክንያት ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ጫና በማሳደሩ የባሕር በር የሌላቸው ሀገሮች ሊደርሱበት ከሚችሉት አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት በ20 በመቶ ያነሰ ቦታ ላይ እንዲገኙ ማድረጉን ጥናቶች እንደሚያመላክቱም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በየዓመቱ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ለወደብ ኪራይ ብቻ እንደምታወጣ ያስታወሱት አቶ ሀብታሙ፤ ይህም የኢትዮጵያ የግማሽ ዓመት የነዳጅ ወጪ መሸፈን የሚችል ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም የባሕር በር ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት ኢትዮጵያ የባሕር በር ልታገኝ የምትችልበትን ሰላማዊ መንገድ ሁሉ መሞከር አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ በሰጥቶ መቀበል መርሕ የባሕር በር ባለቤት የምንሆንበትን ሰላማዊ መንገድ ሁሉ መሞከር እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

# ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች ሀገራዊ ችግሮችን መፍታት ስምን ተሳናቸው?

**ማርቆስ በላይ**



ኢትዮጵያውያን ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበት ዘመናትን ያስቆጠረና የዳበረ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ሥርዓት አላቸው። ለአብነትም በኦሮሞ ጃርሱማ፣ በአማራና ትግራይ ሽምግልና፣ በሲዳማ አፍኒ፣ በጋሞ ዱቡሻን መጥቀስ ይቻላል።

እነዚህ ሥርዓቶች በግለሰብ፣ በቡድንና በማኅበረሰብ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ግጭቶች ወደ ከፋ ሁኔታ ሳይሸጋገሩ በሰላም ለመፍታት ጥቅም ላይ ሲውሉ ቆይተዋል አሁንም እየተሠራባቸው ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ሀገራዊ ምክክር እንዲካሄድ እየተደረገ ነው። በመሆኑም እንደሀገር ላጋጠሙ ችግሮች ሀገር በቀል ችግሮችን መፍቻ ሥርዓቶችን መጠቀም እንደሚገባ ብዙዎች ይስማሙበታል።

ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በግለሰብና በማኅበረሰብ መካከል የሚያጋጥሙ ግጭቶችን ከመፍታት ባለፈ ሀገራዊ ችግሮችን የመፍታት አቅም እንዳላቸው በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ በሶሾሎጂ ትምህርት ክፍል መምህር አሸናፊ መብራቱ ይገልጻሉ፡፡

ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ዘመን ተሻጋሪና ዘመናዊ የአስተዳደር ሥርዓት ባልነበረበት ዘመን ጭምር ለረጅም ዘመናት ግጭቶችን ሲፈቱ ቆይተዋል። በአሁኑ ጊዜ ያሉበት ደረጃና ጥንካሬቸው አጠያያቂ ቢሆንም በማኅበረሰቡ ዘንድ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

ሀገር በቀል የግጭቶች መፍቻ ሥርዓቶች ከዘመናዊው ሥርዓት፣ ግሎባላይዜሽን መስፋፋት፣ ከፖለቲካ ርዕዮት ጫና አሳድሮበታል።ነገር ግን በተለይም በኢትዮጵያ ጫናዎችን ተቋቁሞ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ሥርዓቶቹ ሀገር በቀል በመሆናቸው፣ ከኅብረተሰቡ የመነጩና፣ ሲተዳደርባቸው የቆዩ በመሆናቸው በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ሚና የጎላ ነው ያሉት መምህሩ፣ በየአካባቢው የሚገኙ ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ሥርዓቶችን እንደአስፈላጊነታቸው በማዕከል ደረጃ ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ እንደሆነ ያመላክታሉ።

ሀገር በቀል የግጭቶች መፍቻ ሥርዓቶች በሀገሪቱ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ለመፍታትም የሦስተኛ አካላትን ተፅዕኖ ማስቀረት ያስፈልጋል። ሥርዓቱ ባሕሉን ጠብቆ፣ ጤናማና ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ከመተግበር በዘለለ በሦስተኛ ወገን ጣልቃ የሚገቡ ጉዳዮች በገቡ ቁጥር የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው አስረድተዋል፡፡

በየአካባቢው የሚገኙ ሥርዓቶችን ለሀገር ትሩፋት እንዲሆኑ ሥርዓቶቹን ወደ ፊት በማምጣትና ጥቅም ላይ ማዋል እጅግ አስፈላጊ ነው። በተለይም የድንበር፣ ከመሬት፣ ግጦሽ፣ የእርስ በርስና የቡድን ግጭቶችን ለመቅረፍ ሀገር በቀል ሥርዓቶች ጥቅማቸው የጎላ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

እንደሀገር የግጭቶች መፍቻ ሥርዓቶችን ወደ ማዕከል የማምጣት ሂደት ላይ አንድ አካል ቢኖር መልካም ነው። በዚህ ረገድ እነዚህን ሥርዓቶች ያስፈፅማሉ የሚባሉት የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ እናቶችና አባቶች፣ ሚዲያ፣ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ሰዎች ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች ጫና እየደረሰባቸው በመሆኑ ትውልዱ ወደ ባሕሉ እንዲመለስ ማስተማር፤ መንግሥትም ለሀገር በቀል የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በፖሊሲ የተደገፈ እውቅና መስጠትና ጥበቃ ማድረግ እንደሚገባውና ወጣቱ ትውልድ ለታላላቆች ክብር መስጠትና ትክክለኛ የሆነውን ሥርዓት በማክበር ኃላፊነትን መወጣት እንደሚጠበቅበት ይገልጻሉ።

ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ሥርዓቶች ከግለሰብ ባለፈ ትላልቅ ሀገራዊ ጉዳዮችን መፍታት አቅም እንዳላቸው የሰላምና ግጭት አፈታት ባለሙያ መምህር አብዮት ኑርልኝ ይገልጻሉ፡፡

የግጭት አፈታት ሥርዓቶች የጋራ ስምምነትን ለማምጣት፣ እሴትና ባህል መሠረት አድርገው ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው። በተለይም የተረጋጋ ሰላምን ለማስፈንና እውነትን መፈለግን ዓላማ ያደረጉ ናቸው ይላሉ፡፡

ቀደምት ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በዘመናዊው የመበረዝ፣ መሪ አባቶች ፍትሕንና ሚዛናዊነትን አጣምረው አለመያዝና የአተገባበር ችግር ይታይባቸዋል። በመሆኑም የበፊቱን ባሕልና እሴት በተከተለ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ ለሀገራዊ ችግሮች መፍትሔ ማምጣት ይቻላል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ባሕላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶችን በትምህርት መልኩ መስጠት፣ ማኅበረሰቡ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠርና ሥርዓቱን ለማጠናከር የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባቸውም አመላክተዋል።

# በጣና ሐይቅ ላይ የዓሣ ግብርናን የማስፋፋት ሥራ እየተሠራ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በዓሣ አስጋሪዎች በጣና ሐይቅ ላይ እየደረሰ ያለውን ጫና ለመቀነስ የዓሣ ግብርናን የማስፋፋት ሥራ እየተሠራ መሆኑን የባሕርዳር ዓሣ እና ሌሎች የውሃ ላይ ሕይወት ምርምር ማዕከል አስታወቀ። ከ200 ሺህ በላይ የዓሣ ጫጩቶች እንደሚሰራጩ ተገልጸዋል።

የምርምር ማዕከሉ ዳይሬክተር እና የማኅበራዊ ምጣኔ ሀብት ተመራማሪ አቶ እሪቁ አስማር ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በጣና ሐይቅ ላይ የሚስተዋለው የሕገ ወጥ ዓሣ አስጋሪዎች እንቅስቃሴ የሐይቁን የዓሣ ሃብት አሳሳቢ ደረጃ ላይ በማድረሱ በሐይቁ ላይ እየደረሰ ያለውን ጫና ለመቀነስ የዓሣ ግብርና የማስፋፋት ሥራ እየተሠራ ነው።

ለአካለ መጠን ያልደረሱ የዓሣ ጫጩቶች በሕገወጥ መንገድ በአስጋሪዎች ከውሀ አካላት እየወጡ በመሆኑ የዓሣ ብዝኃ ሕይወት በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ችግሮች ተለይተው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ አቶ እሪቁ ገለጻ፤ የምርምር ማዕከሉ በተለይ የዓሣ ጫጩቶችን በሰው ሠራሽ መንገድ በማስፈልፈል ሁሉም በየቤቱ ዓሣ ማስገር እንዲችል የዓሣ ጫጩቶችን በማባዛት ወደጣና ሐይቅ ከመጨመር በተጨማሪ፤ በክልሉ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ጽሕፈት ቤት በኩል በወረዳዎችና በቀበሌዎች ለአርሶ አደሩ የማከፋፈል ሥራ እየተሠራ ነው።

ባለፈው በጀት ዓመት 733 ሺህ በላይ የዓሣ ጫጩቶችን በማባዛት ወደጣና ሐይቅ የመልቀቅና ለአርሶ አዶሩ የማሰራጨት ሥራ መሠራቱን አስታውሰው፤ በሚቀጥለው ሳምንት ከ200 ሺህ በላይ የዓሣ ጫጩቶችን እንደሚሰራጩ ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

ይህ ተግባር በፓኬጅ የሚሠራ ሲሆን አንድ አርሶ አደር በቀላሉ በሚያዘጋጀው የሦስት መቶ ካሬ ሜትር ኩሬ ላይ 900 ዓሣዎችን በቤቱ ማርባት እንደሚያስችለው አውስተዋል።

በዓሣ የመራቢያ ወቅት ማስገር፣ የአካባቢ መራቆት፣ የዓሣዎች መራቢያ ስፍራ ምቹ አለመሆን፣ ከሱዳንና ከግብፅ በሕገወጥ መንገድ ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ የማስገሪያ መረቦችና የእንቦጭ አረም መስፋፋት ለዓሣ ሃብቱ መመናመን ዋነኛው ምክንያቶች መሆናቸውን አንስተዋል።

እንዲሁም የዓሣ ማስገር ሥራ አብዛኛውን ጊዜ የሚከናወነው በሌሊት በመሆኑ ለቁጥጥር አዳጋች እንዳ ደረገውም ዳይሬክተሩ አክለዋል።

ከዚህ ቀደም አንድ ጀልባ በአማካይ እስከ 67 ኪሎ ዓሣ ያሰግር እንደነበረ አስታውሰው፤ ይህም በቅርቡ በተሠራ ጥናት ወደሦስት ኪሎ መውረዱን ያነሱት አቶ እሪቁ፤ የሚመለከተው አካል ችግሩን ለመቅረፍ ሊረባረብ እንደሚገባና አስጋሪዎችም በኃላፊነት ሊያሰግሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የቁም እንስሳት ሀብትን ከሕገወጦች የመታደጉ ሥራ ጊዜ ሊሰጠው አይገባም!

በእንስሳት ሀብቷ ከዓለም ግንባር ቀደሞቹ ከአፍሪካ ቀዳሚዋ ኢትዮጵያ ከዚህ ሀብት የሚገባትን ያህል እየተጠቀመች ስለአለመሆኗ ሁሌም ይገለጻል፡፡ ለዚህ ደግሞ በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ቢችሉም፣ አንዱ መሠረታዊ ችግር ኮንትሮባንድ ነው፡፡

ሀገሪቱ የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሰፋፊ ጥረቶችን እያደረገች መሆኗ ይታወቃል፤ በብዙ ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የኮንትሮባንድ ሸቀጦችን በቁጥጥር ስር እያዋለች ትገኛለች፡፡ ችግሩን ለመፍታት ዘርፈ ብዙ ጥረት እየተደረገ ባለበት ሁኔታም የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴው መሰረታዊ ችግር ሆኖ መቀጠሉን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የድንበር ተሻጋሪ ሕገወጥ ንግድ በሀገሪቱ የቁም እንስሳትና ሌሎች የግብርና ምርቶች ንግድ ላይ እያሳደረ ያለውን ተጽእኖ አስመልክቶ ያካሄደውና ሰሞኑን ይፋ የተደረገው ጥናትም ይህ ችግር ሀገሪቱን ከቁም እንስሳት ሀብቷ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ እንዳትሆን እያደረጋት ስለመሆኑ ቁልጭ አድርጎ አሳይቷል፡፡

ጥናቱ በየሩብ ዓመቱ ከ106 ሺ በላይ የቁም እንስሳት በሕገወጥ ንግድ ከሀገር እንዲወጡ እየተደረገ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ይህ አሀዝ ለማሳያነት ጥናት በተደረገበት በምሥራቁ የኢትዮጵያ ክፍል ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ በሕገወጥ መንገድ ከሀገር እንዲወጡ እየተደረጉ ያሉት የቁም እንስሳትና ሌሎች የግብርና ምርቶች ውጤቶች በሕጋዊ መንገድ ከሚወጣው ተመሳሳይ ሀብት እንደሚበልጥም ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

ጥናቱ በምሥራቁ የሀገሪቱ ድንበር በሕገወጥ መንገድ እንዲወጡ የሚደረጉትን የቁም እንስሳት ብቻ የተመለከተ ነው፡፡ የሰሜን፣ የደቡብና ምእራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች በጥናቱ ቢካተቱ ደግሞ የጉዳቱ መጠን ከዚህም በእጅጉ ሊልቅ እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ይህ የሩብ ዓመት አሀዝ በዓመት ሲሰላ ከ420 ሺ በላይ የቁም እንስሳት በሕገወጥ መንገድ ከሀገሪቱ እንዲወጡ ይደረጋል ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

ለዚህ ሕገወጥ ተግባር ገፊ የተባሉ ምክንያቶችም ተጠቁመዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል የተቀባይ ሀገሮችን ፍላጎት የሚያሟላ የተስተካከለ የኳረንታይን ሥርዓት አለመኖርና ያሉትም ቢሆኑ አቅማቸው የደከመና አገልግሎት የሚሰጡ አለመሆናቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ጥናቱ መፍትሔ ያለውንም ጠቁሟል፡፡

ለአንድ ችግር መፍትሔ ለማግኘት ችግሩ በሚገባ መለየቱና የመፍትሔ ሃሳብ መመላከቱ ችግሩን መፍታት እንደመጀመር ሊቆጠር ይችላልና ጥናቱ ችግሩን ቁልጭ አድርጎ ማሳየቱና መፍትሔ ማመላከቱን ችግሩን ለመፍታት የተወሰደ አንድ ርምጃ አድርጎ መመልከት ይቻላል፡፡

ይህን ጥናት መሠረት አድርጎ ዘላቂ መፍትሔ ማስቀመጥ ቀጣዩ ትልቅ ሥራ ሊሆን ይገባል፡፡ ችግሩን የመፍታቱ ሥራ እዚህ ላይ እንዳይቆም አጥብቆ መሥራት ግን ያስፈልጋል፡፡ ሀገሪቱ እጅግ ትልቅ ሀብት እንድታጣ እየተደረገች ትገኛለች፡፡

ገፊ ምክንያቶቹ ምንም ይሁኑ ምን በየዓመቱ ይህን ያህል የቁም እንስሳት ሀብት በሕገወጥ መንገድ ከሀገር እንዲወጣ መደረጉ በሀገር ላይ እጅግ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳል፡፡ የሀገሪቱ ቄራዎች / ለሀገር ውስጥም ለውጭ ገበያም ሥጋ የሚያቀርቡት ቄራዎች/ የሚፈልጉትን ያህል ከብት ማግኘት እንዳይችሉ ወይም የከብት ገበያ ውድነት እንዲከሰት ሊያደርግ አይችልም ተብሎም አይታሰብም፡፡

የሀገሪቱን የቁም እንስሳት ከዚህ ሕገወጥ ንግድ ለመታደግ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ኳረንታይኖች እየገነቡ ስለመሆናቸው ከዓመታት በፊት ሲገለጽ ነበር፡፡ አሁን ይህ ጥናት ያወጣው መረጃ ግን የተቀባይ ሀገራትን ፍላጎት የሚያሟላ የተስተካከለ የኳረንታይን ሥርዓት በሀገሪቱ አለመኖሩን አጋልጧል፤ ከዚህ ሁሉ መረዳት የሚቻለው ቀደም ሲል የነበረው ችግር አሁንም መቀጠሉን ነው፡፡

መንግሥት የኮንትሮባንድ ንግድን በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽንና በሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በኩል ለመቆጣጠር እየሠራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ባለፈው ዓመት ወርቅና ሌሎች ሕገወጥ ንግዶችን ለመቆጣጠር የሚሠራ ግብረ ኃይል ከተለያዩ ተቋማት በማውጣጣት አቋቁሞ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በዚህም በተለይ በወርቅ ሕገወጥ ግብይትና ማምረት ተግባር የተሰማሩ አካላትን በቁጥጥር ማዋል የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፤ ይህን ተከትሎም ለብሔራዊ ባንክ በሚገባው የወርቅ መጠን ላይ ለውጥ ማምጣት መቻሉን ከወርቅ አልሚ አካባቢዎች የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ይህን ዓይነቱ ርምጃ የቁም እንስሳት በሕገወጥ መንገድ ከሀገር በሚያስወጡ አካላት ላይም መደገም ይኖርበታል፡፡ በእርግጥ ይህ ጊዜያዊ መፍትሔ ይችላል፡፡ በዚህ ብቻ የተወሰነውን የሀገሪቱን የቁም እንስሳት ሕገወጥ ንግድ መቆጣጠር ይቻላል፡፡ ሕገወጦች ይህን ያህል የሀገር ሀብት ከሀገር እያወጡ መቀጠል እንዳይኖርባቸው ማድረግ ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ከእስከ አሁኑም በላይ ሀብት ሀገር ታጣለች፡፡

ችግሩ ግዙፍ እና ሀገሪቱን ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት እያሳጣ ያለ እንደመሆኑ ዘላቂ መፍትሔን ይፈልጋል፡፡ ዘላቂው መፍትሔ ግን በግብይቱ ሥርዓቱ ላይ አለ የተባለውን ችግር ቀርቦ መፍታት፣ ደረጃውን የጠበቀ ኳረንታይን እንዲኖር ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባሮች ሊሆኑ ይገባል፡፡ ካረንታይኖች ለይስሙላ የሚገነቡ መሆን የለባቸውም፡፡ የቁም እንስሳት ተቀባይ ሀገሮችን ፍላጎት መሠረት ተደርገው መገንባት ይኖርባቸዋል፡፡

በዚህ ሀብት ላይ እየፈጸመ ያለ ሕገወጥ ንግድ ሀገርን ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት እያሳጣ ስለመሆኑ ይህ ጥናት በሚገባ አመላክቷል፡፡ ይህን ችግር ለመቀነስ የሚወጣ የትኛውም መጠን ያለው ሀብት ችግሩን በማስቀረት ሊተካ የሚችል፣ ከዚያም አልፎ ለሌላ ሀገራዊ ልማት የሚውል ሀብት ማስገኘት የሚችል እንደመሆኑ ይህ ችግር ሆኖ የማይጠቀስበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል፡፡

የቁም እንስሳት ሀብትን ከሕገወጦች የመታደጉ ሥራ ጊዜ ሊሰጠው አይገባም! በመሆኑም የኳረንታይን መሠረተ ልማቶች በተገቢዎቹ ስፍራዎች ላይ መገንባትና በሕገወጦች በቀላሉ ሊረበሽ የማይችል የግብይት ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለወገኖቻችን ሰብአዊ እርዳታ በወቅቱ ለማድረስ የሁላችንም ርብርብ ወሳኝ ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

የሰብአዊ እርዳታ የሚለው ቃል በተፈጥሮ አደጋዎች፣ ግጭቶች እና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ለተቸገሩ ሰዎች የሚሰጠውን እርዳታ ያመለክታል። በችግር ጊዜ ህይወትን ለማዳን፣ መከራን ለማቃለል እና የሰውን ልጅ ክቡር ህይወት ለመታደግ ያለመ የድጋፍ ዓይነት ነው።

በሰብአዊነት እና በገለልተኝነት መርሆች የሚተገበር፤ የመጨረሻ ግቡ ለሰው ሰራሽም ሆነ ለተፈጥሯዊ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን በሕይወት ለማትረፍ እና ከድንገተኛ አደጋዎች እንዲያገግሙ ለማስቻል አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶችን፣ አገልግሎቶችን እና ጥበቃ እንዲያገኙ የማድረግ ሂደትም ነው።

በአደጋ ጊዜ፣ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በጎርፍ ወይም በግጭቶች ሳቢያ የሰብአዊ እርዳታ እንደ ምግብ፣ ውሃ፣ መጠለያ፣ የጤና እና የንፅህና መጠበቅያ ያሉ አፋጣኝ ፍላጎቶችን በማስተናገድ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በዚህም ተጨማሪ የህይወት መጥፋትን ለመከላከልም ይረዳል፡፡

አስቸኳይ የህክምና አገልግሎትም በዚሁ የሰብአዊ እርዳታ ውስጥ የሚካተትበት ሁኔታ ያለ ሲሆን ከአደጋዎች ጋር በተያያዘ ሊከሰት የሚችለውን የበሽታ ወረርሽኝ ለመከላከለና ስርጭቱንም ለመግታት ወሳኝ አቅም እንደሚሆን ይታመናል ፡፡

ከዚህም ባለፈ በሰብአዊ ዕርዳታ ማእቀፍ ለአጭር ጊዜ እገዛን በማድረግ ለተጎጂዎች እፎይታ መስጠት ብቻ ሳይሆን በዘላቂነት ካሉበት እንዲያገግሙ እና እንዲቋቋሙ ማድረግ ይቻላል። የተጎዱትን ማህበረሰቦች ከጉዳታቸው አገግመው ራሳቸውን ማስተዳደር እንዲጀምሩ፣ ወደ ነበሩበት የኑሮ ሁኔታ ለመመለስ እና ዘላቂ ልማትን ለማምጣትም የራሱ እገዛ ይኖረዋል፡፡

ከሰብአዊ ርዳታ ቁልፍ መርሆዎች ውስጥ አንዱ ገለልተኛነት ነው። ገለልተኝነት ሰብአዊ ድጋፍን ያለ አድልዎ መከወን ማለት ነው፡፡ ሰብአዊ እርዳታው የተጎጂዎችን ዘር፣ ዜግነት ፣ ሃይማኖት እና የፖለቲካ አስተሳሰብ ያላማከለ፤ ሰው በመሆናቸው ብቻ የሚያገኙት ነው፡፡

የሰብአዊ እርዳታ አገልግሎት በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ እና መርሆዎች የሚመራ ፤ ሴቶችን፣ ህጻናትን፣ አረጋውያንን እና ሌሎች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ ለሲቪሎች ደህንነት ቅድሚያ የሚሰጥ ነው ፡፡ በዚህም የሰዎችን የሰብአዊ መብቶች መከበርን፣ ሰብአዊ ክብር መጠበቅንና ማንኛውንም አይነት አድልዎ፣ ጥቃት ወይም ብዝበዛ መከላከልን ያካትታል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያም በተለያዩ ግዜያት በሚከሰቱ ግጭቶችና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት በተለያዩ ወቅቶች የድርቅ አደጋዎች ተከስተዋል፡፡ በያዝነው አመትም በትግራይ ክልል 32 ወረዳዎች ላይ ድርቅና የምግብ እጥረት ማጋጠሙን የትግራይ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን አስታውቋል፡፡

ታኅሣሥ 10 ቀን 2016 ዓ.ም በታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ የትግራይ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ግብረ መልስ አስተባባሪ አቶ ልጅዓለም ካሕሣይ በክልሉ 32 ወረዳዎች የከፋ ድርቅና የምግብ እጥረት ማጋጠሙን ተናግረዋል። በትግራይ ክልል ደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ መካከለኛውና ሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች የድርቅ አደጋ ያጋጠማቸው መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

በክልሉ የተከሰተው የድርቅ አደጋ በዋነኝነት ከጦርነቱ እና ከተፈጥሮ ጋር ተያይዞ መከሰቱን፤ በዚህም አብዛኛው የክልሉ ነዋሪ እርዳታ ፈላጊ መሆኑንም አስተባባሪው ገልጸዋል፡፡ ያጋጠመው የምግብ እጥረት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለመከላከል በጥቂቱ ለአንድ ዓመት የሚቆይ የእርዳታ አቅርቦት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

በትግራይ ክልል ሁለት ሚሊዮን ዜጎች በድርቅና በግጭት ምክንያት ለምግብ እጥረት መጋለጣቸውን ደግሞ በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ የሆኑት አቶ አታለለ አቡሐይ አመልክተዋል፡፡

በተመሳሳይ በአማራ ክልል በሰሜን ጎንደር፣ ዋግኽምራ፣ የኦሮሞ ብሔረሰብ ሰሜን ሸዋ አካባቢ፣ በምሥራቅ ጎጃም እንዲሁም በአፋር ክልል ወደ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዜጎች በድርቅ እና በሰው ሠራሽ ችግሮች የምግብ እጥረት እንዳጋጠማቸው አስታውቀዋል።

በአሁኑ ወቅት በምግብ እጥረት አደጋ ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች ፤ ሰብአዊ እርዳታዎች በፌዴራል እና በክልል መንግሥታት ፤ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶች ጨምሮ በአካባቢያዊ ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች እየተሰጠ ይገኛል። ከችግሩ አሳሳቢነት አንጻር ግን "የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ" እንዲሉ ሰብአዊ እርዳታው የመላውን ሕዝባችንን ተሳትፎና ርብርብ ይጠይቃል፡፡

የሰብአዊ እርዳታ ለአደጋ ወይም ለችግር ጊዜ የሚሰጥ በጎ ምላሽ ከመሆኑ አንጻር፣ አሁን ላይ በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖቻችንን ሕይወት ለመታደግ ፣ እንደ አንድ ለብሔራዊ ክብሩ ከፍ ያለ ዋጋ እንደሚሰጥ ሕዝብ ብሔራዊ ንቅናቄ መፍጠር ይኖርብናል።

በኢትዮጵያዊ የመረዳዳትና የማካፈል ባህል ያለው ለሌለው ማካፈል ይኖርበታል፡፡ እርዳታውን በማፋጠን የወገኖቻችንን መከራ በማቃለል እና ለተቸገሩት ተስፋ በማምጣት ረገድ ወሳኝ ሚና መጫወትም ይጠበቅብናል።

ከዓመታት በፊት የሰሜኑ የሀገራችን ጦርነትን ተከትሎ ኢትዮጵያ ላይ የተጋረጠውን አደጋ ለመቀልበስ መላው የሀገሪቱ ሕዝብ ርብርብ ማድረጉ አይዘነጋም። በወቅቱ ክልሎች፤ ባለሀብቶች፤ድርጅቶች፤ እና እያንዳንዱ ዜጋ የአቅሙን ያህል እያዋጣ ሕግ የማስከበር ተልእኮውን ደግፏል፡፡

አሁን ሌላ ርብርብና ድጋፍ የሚያሻ የወገናችን ችግር ከፊታችን አግጥጦ ቆሟል ።ችግሩን በስኬት ለመሻገር ለዚህም ከዚህ በፊት እንደታየው የመላው ሕዝባችን ርብርብና ትብብር ወሳኝ ነው፡፡

ከምግብ አቅርቦት በተጨማሪ ከችግሩ ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉ የጤና ችግሮችን ጎን ለጎን በልዩነትም ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ማለትም ለጉዳት የተጋለጡ ሕፃናት፤ ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ ሴቶችና አረጋውያን፤ ነፍሰጡር እናቶች ፤ አካል ጉዳተኞች እና ከባድ የጤና ችግር ያለባቸው፤ ልዩ የሕግ ጥበቃና ከለላ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች በልዩነት ድጋፍ ሊደረግላቸውም ይገባል፡፡

ሰብአዊም፤ ቁሳዊም እርዳታ መስጠት ፤ እንደ ምግብ፣ መጠለያ እና ህክምና የመሳሰሉ መሰረታዊ ፍላጎቶችን ከማቅረብ በተጨማሪ የትምህርት፣ የኑሮ ድጋፍ እና የስነ-ልቦና አገልግሎቶችን መስጠት ያካትታል።

ኢትዮጵያውያን ሰብአዊ እርዳታን በሰብአዊነት ለተቸገሩ ወገኖች የማድረስ ሂደት የረጅም ጊዜ እና የቆየ የመረዳዳት ባህላችንን በተለያዩ ጊዜያት በግልጽ የታየ ነው። በዚህም በባለፈው የኮቪድ ወረርሽኝ ጊዜ በመንግሥትና በግለሰቦች ሲደረግ የቆየው የመረዳዳት ባህላችን አሁንም በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከሰተው ድርቅና የምግብ እጥረት ሊደገም የሚገባው ተግባር ነው።

አስቸኳይ ሰብአዊ እርዳታን የማድረግና ያለማድረግ ጉዳይ ባለ ድርሻ አካላቱ እከሌ ከእከሌ ሳይባል የሁላችንም ነው። ለተከሰተው ችግር ምላሽ መስጠት የአንድ ወገን ተግባርና ኃላፊነት ሳይሆን የሁላችንም ነው። “ለወገን ደራሽ ወገን ነው፡፡ የሚለውን የኖረ አባባል በተግባር ማሳየት ያለብን እኛው ነን። በመሆኑም ሁላችንም የሰብአዊ ድጋፍና እርዳታው ተግባር ልንደግፍ ይገባል!!

ዜና

# የካፒታል ገበያ- ኢኮኖሚን የማሳደግ አንዱ ስልት

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያን ለማስጀመር አዋጅ ተዘጋጅቶ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባ ዓመት አልፎታል። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የካፒታል ገበያ እንቅስቃሴን ለማስጀመር የፀደቀውን አዋጅ ወደ ተግባር የመቀየርና ባለሥልጣኑን የማደራጀት ሥራ ሲያከናውን ቆይቷል። በአሁኑ ወቅትም የሕግ ማዕቀፍ እና መመሪያ ተዘጋጅቶ አስራ አምስት አሻሻጮች ፍቃድ የሚያገኙበት አሠራር ተዘርግቷል።

የካፒታል ገበያ ለልማት ያልዋሉ ገንዘቦችን በማሰባሰብ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገትና ብልጽግና እንዲውሉ የማድረግ፤ ይህንንም ተከትሎ ዜጎችም በአቅማቸው በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ተሳታፊ በመሆን ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችል መሆኑም ይነገራል። ለመሆኑ የስቶክ ማርኬት ወደትግበራ መግባት ለአጠቃላይ የሀገር ኢኮኖሚ እድገት ብሎም ለዜጎች ተጠቃሚነት የሚኖረው ፋይዳ ምንድን ነው?

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚ ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ተኪኤ ዓለሙ(ዶ/ር) የስቶክ ማርኬት መቋቋም ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው ይላሉ። ባለሙያው እንደሚያብራሩት ስቶክ ማርኬት ማለት ተቋማዊ በሆነና በተደራጀ መንገድ የአንድ ድርጅት ድርሻ በአክስዮን ወይንም ቦንድ መልክ የያዙ የገንዘብ ሰነዶች ግብይት የሚፈጸምበት ቦታ ማለት ነው። ሰነዶቹን የሚያቀርበው ድርጅት መንግሥታዊ ወይንም የግለሰብ ሊሆን ይችላል። የሚሸጡት ሰነዶችም የተለያዩ ማለትም የአጭርና የረጅም ጊዜ፤ እንዲሁም በወለድና በብድር መልክ ለግብይት የሚቀርቡ ሊሆኑ ይችላሉ።

በኢትዮጵያ ከዚህ በፊት የአክስዮን ግብይት ልምዱ ቢኖርም በአንድ ወገን ተመኑ ሻጮች ያወጡት ብቻ የሚተገበር ሲሆን በሌላ በኩል አንዳንድ ግዜ ገዥው በፈለገ ግዜ አትርፎ መሸጥ የማይችልባቸው አካሄዶችም ስለነበሩ ትክክለኛ የአክስዮን ገበያ ነበር ለማለት አይቻልም። በመሆኑም መንግሥት ሕጋዊ አደረጃጀት ያለው ተቋም መፍጠሩ ትክክለኛውን አክስዮን በትክክለኛው ዋጋ በተፈለገ ግዜ ለመግዛት፤ ለመሸጥ ብሎም ማስተላለፍ የሚያስችል ታማኝ ምሕዳር እንዲፈጠር ያደርጋል ብለዋል።

ይህም ሰዎች ትንሽም ቢሆን ያላቸውን ገንዘብ በመጠቀም አክስዮን ለመግዛት የሚያስችላቸው ሲሆን በተመሳሳይ መሸጥ በፈለጉም ግዜ ያለምንም ውጣ ውረድ የሚገባቸውን ዋጋ አግኝተው እንዲሸጡ የሚያስችላቸው ይሆናል። በዚህ ሂደትም የገንዘብ ዝውውር እንዲጨምር የሚያደርግ ሲሆን ይህም እንደ ሀገር ለኢኮኖሚ እድገት የራሱ አወንታዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል ሲሉም አብራርተዋል።

ተኪኤ(ዶ/ር) ሂደቱን አስመልክተው እንዳብራሩትም በዓለም ያለው ተሞክሮ እንደሚያሳየው ስቶክ ማርኬት በግለሰቦችም በመንግሥትም የሚደራጅ ሲሆን በኢትዮጵያ ግን ያለው በመንግሥት ስር የተቋቋመ ነው። ስቶክ ማርኬት ሲቋቋም ገዢውና ሻጩ በሕጋዊ መንገድ ብቻ እንዲንቀሳቀሱ በተለይም የገዢው ደህንነት እንዲጠበቅ ያስፈልጋል። ለገበያ የሚቀርበው አክስዮንም የተረጋገጠ ታማኝ ከሆኑ ኩባንያዎች መሆን ይጠበቅበታል። በመሆኑም ይህንን ምሕዳር ለመፍጠር አሁን ባለው ሁኔታ ተገቢ የሆኑ ሕጎች የማውጣትና የመቆጣጠር ኃላፊነት መንግሥት መያዙ ተገቢ ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ የምጣኔ ሀብት ባለሙያና አማካሪ የሆኑት ሞላ ዓለማየሁ(ዶ/ር) በበኩላቸው በሚቀጥሉት ዓመታት የግሉ ዘርፍ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ትልቁን ድርሻ ይይዛል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ ገልጸዋል።

በመንግሥት ወይንም በግለሰቦችና በጥቂቶች ጥምረት ብቻ የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ተይዞ የትም ሊደርስ አይችልም ያሉት ሞላ(ዶ/ር)፤ የስቶክ ማርኬት መቋቋም ዜጎች ባላቸው አቅም ከኢኮኖሚው ተሳታፊም ተጠቃሚም እንዲሆኑ ያስችላል ይላሉ።

ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ያደጉ፤ እያደጉ የመጡና ማደግ የሚፈልጉ በስቶክ ማርኬት ውስጥ ለመንቀሳቀስ አቅሙም አደረጃጀቱም ያላቸው በርካታ ኩባንያዎች አሉ። እነዚህ ኩባንያዎች ለማደግ ደግሞ ከፍተኛ ካፒታል ያስፈልጋቸዋል። በሀገሪቱ ያሉት እንደ ባንኮች ያሉና ሌሎች የፋይናንስ አበዳሪ ተቋማት ደግሞ ያላቸው ሀብት ውስን ነው። የስቶክ ማርኬት መፈጠር እነዚህ ተቋማት ከሕዝቡ በትንንሽ መጠን የሚሰበሰብ ከፍተኛ ገንዘብ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ይሆናል። እነዚህ ክፍተቶች በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ስቶክ ማርኬትን ለመተግበር የሚያስችል ምቹ የኢኮኖሚ ምሕዳር መኖሩንም የሚያመላክት ሁኔታ ነው ሲሉም አብራርተዋል።

ሞላ(ዶ/ር) እንዳሉት፤ በሀገሪቱ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን መቋቋሙም ለአክስዮን ገዢዎች ብዙ ጥቅም አለው። አንደኛው ሰዎች እነሱ ላሰቡት የንግድ እንቅስቃሴ የማይበቃ ገንዘብ ካላቸው የትም አልደርስም በሚል እንዳያባክኑት በር ይከፍታል። በተጨማሪ በአክስዮን ሽያጭ የሚገኝ ወለድ ከሌሎች ፋይናንስ ተቋማት የተሻለም ነው። ይህ በተዘዋዋሪ የኑሮ ውድነትንም የሚቀርፍ ብሎም ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር የሚጠቅምና ዜጎች ከሀገር አድገት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችልም ነው። ስቶክ ማርኬት ላይ የገባ ኩባንያ ፈቃድ ሲያገኝ ችግሮቹንና መልካም አጋጣሚዎችን በግልጽ ስለሚያሳይና ድርጅቶቹ ያሉበት አቋም ስለሚታወቅ ከመጭበርበር ይታደጋል።

ባጠቃላይም የስቶክ ማርኬት መተግበር የገበያ መስፋፋትን በመፍጠር የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲያድግ ዘመናዊ የሆነና የተቀላጠፈ አሠራር እንዲፈጠር ይረዳል ያሉት ምሑራኑ፤ ይህም ሆኖ ከሕግ መውጣት ጀምሮ

# በኢትዮጵያ በየዓመቱ 19 ሚሊዮን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ከሚመረተው ከ31 ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ከ19 ሚሊዮን በላዩ አገልግሎት ላይ እየዋለ አይደለም፡፡

ይህ ምርት ወደገበያ ቢገባ ለሀገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት በተጨማሪ የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን እንደሚፈጥር ያነሱት አቶ አስመላሽ፤ በየቱቦውና በየመንገዱ ቆዳን መጣል በማቆም ሀገር እንድትጠቀም ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት ይጠይቃል ብለዋል፡፡

ይህን ችግር ለመፍታት በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ችግሮችን በመፈተሽ ለእያንዳንዱ መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል፤ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ችግሮችን በመለየት የየዘርፉ ባለድርሻ አካላትን ባሳተፍ መልኩ ወደሥራ ከተገባ ለችግሩ መፍትሔ እንደሚመጣ ዴስክ ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ዘርፉን መደገፍና ማልማት፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የገበያ ሥርዓቱን በማሻሻል ረገድ የየራሳቸው ድርሻ ያለ ሲሆን፤ ምርቱን ተቀብሎ ለውጭ ገበያ የማቅረብ፣ የፋብሪካዎችን አቅም መገንባት፣ የፖሊሲ ማሻሻያ እንዲደረግ ግፊት መፍጠርና ሌሎች ስልታዊ ጉዳዮችን ቀርጾ የኤክስፖርት አቅም የማሳደግ ድርሻ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መሆኑን አመላክተዋል፡፡

እንደ አቶ አስመላሽ ገለጻ፤ ችግሮቹን በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ ለመስጠት በፌደራል ደረጃ ከኢንዱስትሪ፣ ከንግድና ከግብርና ሚኒስቴር የጥናት ቡድን ተዋቅሮ ከጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢና ከሌዘር አምራች ማኅበራት ጋር በመሆን ጥናት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በጥናቱ እንደሀገር በሥራ ላይ ከነበሩ 7 ሺህ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ ማኅበራት ውስጥ አንድ ሺህ ማኅበራት



በዘርፉ ባሉ ችግሮች ምክንያት ከገበያ መውጣታቸውን ያነሱት አቶ አስመላሽ፤ እነኝህ ማኅበራት ልምድ ያላቸው በመሆኑና ወደዘርፉ ተመልሰው ውጤታማ ሥራ መሥራት የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚገባ አንስተዋል፡፡

ገበያው በግብይት ሥርዓት መመራት እንዳለበትና በዘርፉ ላይ ያሉ አዋጆችንና መመሪያዎችን ወደመሬት ወርደው ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸው አንስተው፤ ገበያው ለሁሉም ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ተደራሽ መሆን ሲችል የተሻለ ምርት ያለው የተሻለ ዋጋ ያገኛል ነው ያሉት፡፡

በተለይም ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ኖሯት ዘርፉ እየተነቃቃ በሚሄድበት ወቅት አቅራቢዎችም የተሻለ ቆዳ የማምረት ፍላጎት ስለሚኖራቸው በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋናዮች አስፈላጊውን ጥረት የሚያደርጉ በመሆኑ የምርቱ ጥራት እየተሻሻለ እንደሚሄድ ተናግረዋል፡፡

ዘርፉ ከጊዜ ወደጊዜ እየወደቀ በመሆኑ የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚያስፈልገው ገልጸው፤ ሁሉም የበኩሉን አስተ ዋፅዖ ሊወጣ እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# በከሠም ግድብ በዓመት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ፋብሪካው ለአካባቢው ማኅበረሰብና ለሠራተኞች በራሱ ሁለት ሱቆች ከመደበኛው ገበያ በግማሽ ባነሠ ዋጋ ምርቶቹን እየሸጠም ይገኛል። ባጠቃላይ በፋብሪካው የእርሻ ሥራ ከተሠማሩት መካከል ከ65 በመቶ በላይ የአካባቢው ነዋሪዎች ናቸው። አካባቢው ከፍተኛ የማምረት አቅም ያለው በመሆኑና ለውጪ ገበያ ሊቀርብ የሚችል አቅም ስለሚኖር ከማኅበረሰቡ ጋር በመሆን የተጀመረው ሥራ የሚቀጥል ይሆናል።

በተጨማሪም የውሃ መስመር በመዘርጋት መሬት በማልማት የአካባቢው ነዋሪ ሸንኩርት እንዲያለማ እየተደረገ ይገኛል። በዚህም ሳቡሬ በሚባለው አካባቢ 255 ሄክታር በመከለል ለእያንዳንዱ ግለሰብ ግማሽ ሔክታር መሬት ተሰጥቷል። በተመሳሳይ ድቦ በሚባለው አካባቢ በግማሽ ሄክታር ሽንኩራ አልምተው ለፋብሪካው እንዲሸጡ በሩብ ሄክታር ሽንኩርት ወይንም የመረጡትን የጓሮ አትክልት እንዲያለሙ ተደርጓል።

ፋብሪካው በአካባቢ ጥበቃ ረገድም በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል ያሉት አቶ ሠለሞን በሁለት ቦታዎች ችግኝ በማፍላት በየዓመቱ በነፃ ለአካባቢው ማኅበረሰብ እያቀረበ ይገኛል። የሚቀርቡት ችግኞችም በድርቅ ወቅት ለእንስሳት መኖነት የሚውሉ ተክሎች ናቸው። በዛፍነት የሚተከሉም በረሃማነትን የሚከላከሉ ውሃ የሚይዙና ድርቅ ሲከሠት የመቋቋም አቅም ያላቸው መሆናቸውን ገልጸዋል።

# በክልሉ የየብስ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እንቅስቃሴዎችን ሙሉ ለሙሉ ለማስጀመር ሰፊ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አመላክተዋል።

በተጀመረው ሠላም የየብስ ትራንስፖርት ከተለያየ አቅጣጫ መምጣት ጀምሯል ያሉት ኃላፊው፤ በቀጣይ ተጠናክሮ ተግባራዊ በሚደረገው የሠላም ሁኔታ የሕዝብ ትራንስፖርት ሙሉ ለሙሉ እንዲጀመር እየተሠራ እንዳለ ተናግረዋል። በተለይ የገና በዓል መዳረሻ ቀናት ውስጥ ብዙ ነገሮች እንደሚስተካከሉ ጠቁመው፣ እንግዶች በየብስም ሆነ በአየር የትራንስፖርት አማራጮች ወደ ክልሉ መምጣት እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

በአሁን ወቅት የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ከአዲስ አበባ፣ ባሕር ዳር፣ ጎንደር ላሊባላ እየተሰጠ እንዳለ በመጥቀስ፤ አሁን ደግሞ ከባሕርዳር ላሊበላና ጎንደር አገልግሎት እንዲሰጥ ጥረት እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

በመንገድ ትራንስፖርት በተለያየ መንገድ ተጀምረው የቆሙት ዳግም መጀመራቸውን ጠቅሰው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተጎዱ መንገዶች ጥገና እንዲደረግ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ኃላፊው አክለው እንደተናገሩት፤ የፀጥታ ኃይሉ የአካባቢውን ሠላም ለማስጠበቅ እየሠራ ይገኛል። በአሁን ወቅት አልፎ አልፎ ከሚያጋጥሙ ችግሮች ውጪ በአንጻራዊነት በብዙ ቦታዎች ላይ ሠላም ሰፍኗል። የሚገጥሙ ችግሮችንም የፀጥታ ኃይሉ እየተከታተለ ከምንጫቸው ለማድረቅ እየሠራ ይገኛል።

በተለያዩ የውጭ ሚዲያዎች የሚሰማውና መሬት ላይ ያለው እውነታ ይለያያል ያሉት ዶክተር መንገሻ፤ ኅብረተሰቡ ለራሱ የፀጥታው ባለቤት ሆኖ መረጃዎችን እየሰጠ፣ ችግር ያለባቸውን አካላት እያጋለጠ እንደሚገኝ፤ በዚህም በርካታ ሰዎች በቁጥጥር ሥር እየዋሉና ሠላም እየሰፈነ እንዳለ ተናግረዋል።

ሆኖም በውጪ ያሉ ሚዲያዎች ኢትዮጵያ በቱሪዝም ከዓለም ድርሻዋን እንዳትወስድ የሀገርንና የክልሉን ገጽታ የማበላሸት ተልዕኮ አንግበው እየሠሩ እንዳለ ጠቅሰዋል። የራሳቸው የተለያየ ፍላጎት ያላቸው አካላትም ቱሪስት እንዳይመጣ፣ ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዳይሆን የራሳቸውን ቅስቀሳ እያደረጉ እንዳለ ጠቁመዋል። ይህ ሁኔታ ሀገርንና ሕዝብን የሚጎዳ በመሆኑ በዚህ እኩይ ተግባር ውስጥ የተሰማሩ ወገኖች የሕዝቡን ተጠቃሚነት በማሰብ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሳስበዋል።

ጎብኚዎች ኢንቨስት አድርገው ኢኮኖሚው ላይ የራሳቸውን አስተዋፅዖ አበርክተው በተወሰነ መልኩ መነገራገጭ የሚታይበትን የቱሪዝም ዘርፍ ማበረታታት እንዲችሉ የአካባቢው አመራር፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች ከወጣቶችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር ውይይት ማድረግ መጀመሩንም ተናግረዋል።

ኃላፊው እንዳሉት፤ “ሕዝቡ እየተጎሳቆለ ነው ያለው። የሕዝቡን ጥቅም የሚጎዳ ነገር ውስጥ መግባት ተገቢ አይደለም። ይህ መታረም አለበት። ይህን ለማስተካከል ሥራዎች ተሠርተዋል። በክልሉ የሠላም ጥሪ ተላልፏል። ብዙዎቹ ወደ ሠላማዊ መንገድ መጥተዋል። አንዳንድ የራሳቸውን ፍላጎት በተለያየ መንገድ ጥቅም ማስከበሪያ አድርገው የወሰዱ ኃይሎችና ወደ ሠላማዊ መንገድ ባልመጡት ላይ የሕግ ማስከበር ሥራው እየተሠራ ነው”።

ከኢንተርኔት አኳያ ቱሪስት በሚያስተናግዱ ሆቴሎች የኢንተርኔት መስመር የተለቀቀላቸው እንዳሉ ጠቁመው፤ ሁኔታዎች እየተገመገሙ አገልግሎቱ በአጠቃላይ እንዲኖር እንደሚሠራም አስታውቀዋል።

# የማዳበሪያ አቅርቦት ማነቆ መፍታው ያስገኛቸው ውጤቶች

**አስቴር ኤልያስ**

የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ የመንግሥት ቁልፍ ጉዳይ ነው። ለእዚህም በማዳበሪያ አቅርቦት፣ በማሳና በሜካናይዜሽን እንዲሁም ለሜካናይዜሽን ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር በታመነበት ኩታ ገጠም ማሳ ማስፋፋት ላይ በትኩረት እየተሠራ ይገኛል።

መንግሥት ለምርትና ምርታማነት ማሳደጉ ሥራ ወሳኝ ከሆኑት ግብዓቶች መካከል አንዱ የሆነውን የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ በድጎማ እያቀረበ ይገኛል፤ ለእዚህ የሚመደበው በጀትም ከዓመት ዓመት እያደገ፣ የሚቀርበው የማዳበሪያ መጠንም እንዲሁ እየጨመረ መጥቷል።

ለአፈር ማዳበሪያ የሚያስፈልገውን በጀት በመመደብ ለዘርፉ ምርትና ምርታማነት ማደግ መንግሥት ቁርጠኛ ቢሆንም፣ ማዳበሪያውን በመግዛትና ለአርሶ አደሩ በማቅረብ በኩል ያለው ሂደት እስከ አለፈው የመኸር ወቅት ድረስ ፈታኝ ሆኖ ቆይቷል። በተለይም ፈተናውን ከባድ ሲያደርጉ ከነበሩት ችግሮች መካከል የውጭ ምንዛሪ እጥረትና የማዳበሪያ የግዥ ሥርዓቱ ችግር ያለበት መሆኑ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ችግር በተለይም ያለፉት ሦስት ዓመታት፤ በተለይ ደግሞ የአምናው የመኸር ወቅት የግብርናው ዘርፍ ፈተና ሆኖ ታይቷል። በዚያን ወቅት የአንዳንድ አካባቢ አርሶ አደሮች ማዳበሪያ በወቅቱ እየደረሳቸው ስለአለመሆኑ በስፋት ቅሬታ ያቀርቡም ነበር። በአንጻሩ ማዳበሪያ መያዝ የማይገባቸው አካላት ማዳበሪያውን በሕገወጥ መንገድ ያዘዋውሩ የነበረበት፣ በዋጋ በኩልም እንዲሁ መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ያልተፈጸመበት ሁኔታ ስለመስተዋሉ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ጥቆማዎች ይቀርቡ ነበር።

ይህ የማዳበሪያ ችግርና በግብርና ዘርፉ ላይ አሳድሮት የቆየው ተግዳሮት ዘንድሮ መፍትሔ እንዲያገኝ ተደርጓል። ለእዚህ ውጤት የተደረሰው በጣም በብዙ ፈተና እና ተግዳሮቶች ውስጥ ታልፎ መሆኑንም በቅርቡ መግለጫ የሰጡት የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) አስታውቀዋል። ሚኒስትሩ ግብርና በባሕሪው ሊሻገራቸው የሚገባ ማቆዎች እንዳሉትም ነው ያስታወቁት።

እርሳቸው እንዳሉት፤ የግብርናው ዘርፍ አንዱ ማነቆ የተባለው ጉዳይ ግብርናው የዝናብ ጥገኛ መሆኑ ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ አሁን ባለው የአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ ዝናብ በወቅቱ የማይጥልበት ሁኔታ ሲፈጠር ችግሩን የከፋ ያደርገዋል። አርሶ አደሩም እንደ እስከ አሁኑ ልምዱ ዝናብ ብቻ ጠብቆ የሚያርስ ከሆነ ግብርናውን ለፈተና ተጋላጭ ያደርገዋል። ስለዚህ ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ/ ሥራው በዓመት፣ በሁለትና ሦስት ዓመት ውስጥ የሚሠራ ባይሆንም/ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት መሠራት ይኖርበታል።

ሌላው ማነቆ ሆኖ የቆየው የማዳበሪያ አቅርቦት ነው፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት የማዳበሪያ አቅርቦት የጨመረበት ወቅት ነው ማለት ብቻ ሳይሆን የማዳበሪያ ዋጋም ከእጥፍ በላይ የናረበት ጊዜ ነበር ማለቱ ሁኔታውን ይበልጥ ገላጭ እንደሚያደርገው ሚኒስትሩ ያስረዳሉ። የማዳበሪያ ዋጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ መጨመሩ እንዳለ ሆኖ የእኛ የግዥ ሂደት የተንዛዛ መሆኑ የበለጠ በውድ እንድንገዛ አድርጎናል ሲሉም ሚኒስትሩ ያብራራሉ። በመንግሥት ቁርጠኝነት በግዥ ሥርዓቱ ላይ ለውጥ ማድረግ መቻሉን ጠቅሰው፣ በዚህም ለማዳበሪያ ግዥ ይወጣ የነበረውን ወጪም መቆጠብ መቻሉን ተናግረዋል።

ከሦስት ዓመት በፊት መንግሥት ለማዳበሪያ ግዥ ድጎማ አያደርግም ነበር። በገዛበት ዋጋ ቀጥታ ለአርሶ አደሩ ያስተላልፍ ነበር። አምና 13 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ገዝቶ መንግሥት ድጎማ አድርጓል። በአምናው ዋጋ ማዳበሪያ ገዝተን


ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)

ቢሆን ኖሮ ዘንድሮ 19 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለመግዛት ብዙ ቢሊዮን ብር ያስፈልገን ነበር።

አሁን ተግባራዊ በተደረገው የግዥ ሥርዓት ለውጥ ማዳበሪያ በተመጣጣኝ ዋጋ በሚፈለግበት ጊዜ ገዝቶ ማድረስ ተችሏል። ይህ ብቻ አይደለም ወጪ መቀነስም ተችሏል። መንግሥት ላይ ሊደርስ የሚችለውን የድጎማ ጫናም በጣም በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል። ይህ ሁኔታ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይም የራሱ የሆነ ትርጉም ይኖረዋል።

በቀጣዮቹ ዓመታትም ተመሳሳይ እርምጃዎችን መውሰድ ከተቻለ የተቀነሰው ድጎማ በኢኮኖሚው ውስጥ ገብቶ ለሌላ ዘርፍ ድጋፍ እንዲውል ማድረግ ያስችላል። በግብርና ዘርፍ ውስጥ ለሚከናወኑ ሥራዎች ድጋፎችን ማድረግ እንደሚያስችል ሚኒስትሩ አስረድተዋል።

የግዥው ሥርዓት ከዋጋ አንጻር ያለውን የድጎማ መጠን ቀንሷል የሚሉት የግብርና ሚኒስትሩ፣ የግዥ ሥርዓቱ የመስተካከሉ ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ፋይዳ የአፈር ማዳበሪያን በብዙ መጠን ለመግዛት መርዳቱ መሆኑንም አመልክተዋል። አምና 13 ነጥብ 6 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ መገዛቱን አስታውሰው፣ የአሠራሩ መስተካከል ዘንድሮ 19 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል በመግዛት ለአርሶ አደሩ በስፋት ተደራሽ የማድረግ አቅም ሰጥቶናል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስገባው ማዳበሪያ ብቻ እንዳልሆነም የጠቀሱት ሚኒስትሩ፣ መድኃኒት፣ ነዳጅ እና ሌሎችንም እንደምታስገባ ይገልጻሉ፤ በአፈር ማዳበሪያ ግዥ ላይ የተፈጠረው ብቃት አንደኛ የመንግሥትን የድጎማ ጫና መቀነስ ማስቻሉን ተናግረዋል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ መጠኑ ሰፊ የሆነ ከአምናው አንጻር ሲተያይ ስድስት ሚሊዮን ተጨማሪ ኩንታል ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ጨምረን እንድንገዛ አቅም ፈጥሮልናል ሲሉ አብራርተዋል። በሦስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው ደግሞ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ዋና ተብሎ የሚጠቀሰው የተገዛውን የአፈር ማዳበሪያ በወቅቱና በጊዜው ወደ እርሶ አደሩ ማድረስ መቻሉ መሆኑን አስታውቀዋል።

ሚኒስትሩ እንደሚሉት፤ አምና የነበረው ችግር ማዳበሪያ መግዛት ላይ ብቻ የታየ አይደለም። አርሶ አደሩ ለመዝራት ሲዘጋጅ ማዳበሪያ እርሱ ዘንድ አለመድረሱም ላይ ነው። የተገዛው ማዳበሪያ በሰዓቱ እና በሚያስፈልገው ጊዜ ወደአርሶ አደሩ የማይደርስ ከሆነ የቱንም ያህል በብዙ መጠን ቢገዛ ትርፉ ድካም እንጂ ውጤት አይኖረውም።

አሁን እኛ ፈተና እየሆነብን ያለው ማስቀመጫ ቦታ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ማዳበሪያውን እያስገባን ያለነው ቀድመን ስለሆነ ለአርሶ አደሩ ቶሎ ተደራሽ ካላደረግን የማከማቻ ችግር ሊያጋጥመን ይችላል ብለዋል። ‹‹የምንገዛውን 19 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ማከማቸት የሚያስችል መጋዘን (ቦታ) የለንም። ›› ያሉት ሚኒስትሩ፣ ማዳበሪያውን የምናመጣው ወቅት እየጠበቅን መሆን አለበት ሲሉም ተናግረዋል። ለምሳሌ ለመስኖ የምናመጣውን አርሶ አደሩ ወዲያውኑ ይወስደዋል። ከዚያ መጋዘናችን ክፍት ስለሚሆን ለበልግ ደግሞ እናመጣለን። የበልጉ ቦታ ሲለቅ ለመኸር ይመጣል ሲሉ ያብራሩት ሚኒስትሩ፣ ስለዚህ የምናመጣውን የአፈር ማዳበሪያ በየወቅቱ በመከፋፈል ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል።

ለአብነትም ደቡብ ምዕራብ ክልልን ለእነርሱ መኸር የሚባለው ከሌላው አካባቢ በወቅት ደረጃ የተለያየ ነው። በክልሉ በቆሎ የሚዘራበት ጊዜ የካቲት ወይም መጋቢት አካባቢ ነው። ሌላው አካባቢ ደግሞ የሚሆነው ሚያዚያ ላይ ነው። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት እየገባ ያለው የአፈር ማዳበሪያ ለእነርሱም ጭምር የሚውል ነው ሲሉ ሚኒስትሩ አመልክተዋል።

‹‹በአሁኑ ወቅት የበልግ ማዳበሪያ ሙሉ በሙሉ ተገዝቷል። ስለዚህ ለበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች ማዳበሪያ ቀድሞ መጋዘናቸው ውስጥ ይገኛል። ስለዚህ ማዳበሪያውን መግዛት ብቻ ሳይሆን ሪፎርም ያደረግነው ማዳበሪያ የሚጫንበትንና የሚደርስበትንም ጊዜ ጭምር ነው›› ብለዋል።

ሚኒስትሩ፣ ከዚህ ጋር አያይዘው የጠቀሱት ጉዳይ የአፈር ማዳበሪያን ከሚያጓጉዙ ትራንስፖርተሮች ጋር በቅርቡ የተደረገውን መወያየታቸውን ነው። ‹‹በወቅቱ ከትራንስፖርተሮቹ ጋር በተደረገ ውይይት ከእነርሱ በኩል የተገለጸው ወደ ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገር የሚገባው ምርት የሚበዛባት እና የሚያንስበት ጊዜ መኖሩ ነው›› ያሉት ሚኒስትሩ፣ እኛ ማዳበሪያ የምንጭነው በጥቅምት፣ ኅዳርና ታኅሣሥ ላይ ነው። ትራንስፖርተሮቹ በዚህ ጊዜ ሥራ አልነበራቸውም። እኛ ያደረግነው ይህን አቅም መጠቀም ነው›› ሲሉ ገልጸዋል።

‹‹አምና ሎጅስቲክስ ሁሉ አቁመን ነው ማዳበሪያ ሰኔና ግንቦት አካባቢ የጫንነው›› ሲሉ ሚኒስትሩ አስታውሰው፤ ይህ የተደረገው ሁሉም በአንድ ጊዜ ስለመጣ መሆኑን ተናግረዋል። ‹‹ስለዚህ ዘንድሮ ምንም አይነት የሎጂስቲክስ መንገራገጭ ሳይኖር ቀድመን በማምጣት ያለን የሎጂስቲክስ አቅም ነፃ በሚሆንበት ጊዜ በመጫን ባቡሩን ተጠቅመን ሌሎች የኢኮኖሚ ሥራዎች ላይ ተፅዕኖ በማይኖርበት ሁኔታ መሥራት ችለናል ሲሉ አብራርተዋል።

ግዥያችንን ስላቀድን የትኛውን ማዳበሪያ መቼ እንጫን? የትራንስፖርት እና የሎጂስቲክስ አቅማችን የሀገራችን ይታወቃልና በማይንገራገጭበት ሁኔታ እንዴት እንጫን? የሚለውን ጉዳይ በአሁኑ ወቅት በጣም ትልቅ እፎይታ የሚሰጥ ሥራ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። እውነቱን ለመናገር እንደ እኔ አመለካከት በዚህ ላይ የተሠራው ሥራ ባለፉት አምስት ወራት ሠራን ከምንላቸው ትልቅ ሪፎርሞች ውስጥ እንደ አንዱ ሊቆጠር የሚችል ነው። ምክንያቱም 20 ቢሊዮን ብር መቆጠብ ለኢትዮጵያ በቀላሉ የሚታይ አይደለም›› ብለዋል።

ከዚህ ቀደም ምርጥ ዘርም ሆነ ማዳበሪያ አርሶ አደሩ እንዲወስድ ሁሌም ይጠይቅ እንደነበር አስታውሰው፣ ያኔ ግብዓትን እምብዛም የሚወስድ እንዳልነበረ ገልጸዋል። በዚህ የተነሳም ምርጥ ዘር መጋዘን ውስጥ የሚበሰብስበት፣ በተመሳሳይም የአፈር ማዳበሪያ የሚወገድበት ጊዜ እንደነበር አስታውሰዋል።

ይህ አመለካከት መቀየሩን ጠቅሰው፣ ባለፉት ዓመታት በተሠሩ የኤክስቴንሽን ሥራዎች አርሶ አደሩ “ቴክኖሎጂ አምጡ” የሚልበት ሁኔታ መፈጠሩን መመልከት መቻሉን አስታውቀዋል። አርሶ አደሩ ማዳበሪያውንም ምርጥ ዘሩንም አቅርቡ እያለ ጥያቄ እንደሚያቀርብ ጠቅሰው፣ ማሟላት ያልተቻለው ይህን አርሶ አደሩ ዘንድ የተፈጠረውን ፍላጎት መሆኑን አስታውቀዋል። በቀጣዮቹ ዓመታት ትልቅ ሥራ መሥራት ያለብን በአርሶ እና አርብቶ አደሩ ዘንድ የተፈጠረውን ይህን የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለማሟላት መረባረብ ላይ ይሆናል ብለዋል ።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ለዚህም ነው ማዳበሪያ ላይ ትልቅ ሥራ መሥራት የተፈለገው። ማዳበሪያን በተመለከተ አምና የቀረበው 13 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ኩንታል ነበር። የዘንድሮው ፍላጎት ሲጠና 23 ሚሊዮን ማቅረብ የሚያስችል ፍላጎት እንዳለ ተለይቷል። ለእዚህም ነው 23 ሚሊዮን ኩንታል ለማቅረብ ታቅዶ የነበረው። ይህ አኃዝ ከአምናው የአስር ሚሊዮን ጭማሪ ያለው ነው።

ይህ ፍላጎት ሁሌም የሚገደበው አቅም መሆኑን ሚኒስትሩ ጠቅሰው፣ ቢያንስ ዘንድሮ በተሻለ መንገድ በመግዛታችን ከአምና ያነሰ ሀብት ቢመደብም እንኳ 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ከአምናው የስድስት ሚሊዮን ጭማሪ ያለው ማዳበሪያ እንገዛለን ብለዋል። ይህም በማዳበሪያ አቅርቦት ላይ የተደረገ ትልቅ ጭማሪ ነው ብለን ወስደናል ብለዋል።

ግብርናን ማዘመንን አስመልክተው ሲገልጹም ‹‹አማራጮችን መጠቀም ከቻልን፣ ግብርናችንን ሜካናይዝ ካደረግን፣ ኩታ ገጠምን ሰፋ አድርገን ከሄድንበትና ግብዓት ማቅረብ ከቻልን ግብርናን ማዘመን ከእነዚህ ውጭ ሌላ ነገር የለውም ሲሉ ሚኒስትሩ ተናግረዋል። ‹‹ኢትዮጵያ ይህንን መንገድ ጀምራለች፤ ግብርናዋ ተንቀሳቅሷል። ነገር ግን መድረስ የሚገባት ደረጃ ላይ አልደረሰችም። በእዚህ ሁሉ ውጤታማ ለመሆን የጀማመረቻቸውን ሥራዎች እና ውጤት የተገኘባቸውን ሥራዎች እያሰፋች መሔድ ይጠይቃታል ብለዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ዩኒቨርሲቲዎች ከመማር ማስተማር ባሻገር ...

ግርማ መንግሥቴ

በዚህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ያለ ጥናትና ምርምር ጋት እልፍ ማለት አይቻልም። በመሆኑም፣ ጥናትና ምርምር፣ የጥናትና ምርምሩ ግኝትና ምክረ ሀሳብ (ሀሳቦች) የሁሉም ነገር መሽከርከሪት እንዲሆኑ ዘመኑ ፈቅዶላቸዋል።

እንደ መታደል ሆኖ፣ ዓለም እንደ አጠቃላይ ስትታይ የሰው ልጅ አእምሮ (ያው ጥናትና ምርምር ማለት ነው) መሰልጠንና መራቀቅ ምክንያት ከነበረችበት ዳዴ ተስፈንጥራ ጨረቃ ላይ ወጥታለች። "በምድር ተሽከርካሪ፤ በሰማይ በራሪን መጠሪያዋ ከማድረግም አልፋ ባህሩን በማቋረጥ እስከ መሰርጎድ (ሰርጓጅ መርከቡን አስቡት) ድረስ ረቃ፣ ተራቃለች።

እንዳ አለመታደል ሆኖ ደግሞ፣ በዚህ ባቡር ላይ ያልተሳፈሩ፣ ተሳፍረውም ከሆነ እየተንጠባጠቡ የትም የቀሩ የዓለም አካላት ያሉ ሲሆን፤ ቁጥራቸውም የትየለሌ፣ ችግራቸውም በዛው ልክ የምድር አሸዋን ያህል ሆኖ ኑሮን ("ኑሮ ከተባለ ማለት ነው) እየኖሩት ይገኛሉ።

የጥናትና ምርምር ሥራ ከማይፋታቸው፣ ተነጥሎም ከማይታይባቸው ጉዳዮች አንዱ ትምህርት ነው። ከጥናትና ምርምር በፊት ትምህርት መኖር አለበት። ትምህርት በሌለበት ተመራማሪ አይጠበቅም፤ ከተጠበቀም ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደ መሰማራት ነው የሚቆጠረው። በመሆኑም፣ የትምህርት ሥርዓት ላይ ወገብን ጠበቅ አድርጎ መስራት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው።

ይህ በትምህርት ላይ፣ በተለይም በትምህርት ጥራት ላይ ወገብን ጠበቅ አድርጎ መስራትን በተመለከተ በስፋት ከተሰራባቸውና እየተሰራባቸው ካሉ ተግባራት አንዱና ምናልባትም ዋናው ሲሆን፣ ውጤቱንም በመጠባበቅ ላይ ያሉ በብዙዎች ናቸው።

እንደሚታወቀውም ሆነ የዓለም ተሞክሮ እንደሚያሳየው፣ መጽሐፉም "ሁሉን መርምሩ፤ የተሻለውን ያዙ እንደሚለው፤ ዩኒቨርሲቲዎችም ሲቋቋሙ በየ"ዓላማዎቻቸው ስር እንዳሰፈሩት የትምህርት ጥራት በተጠበቀበት ምህዳር ጥራቱን የጠበቀና የአካባቢ ማህበረሰብን ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማግኘት ብርቅ አይደለም። ማህበረሰብን፣ በተራዛሚውም ሀገርን ከገባበት አረንቋ ጎትተው የሚያወጡ ችግር ፈቺ የጥናትና መርምር ስራዎችን ማግኘት የሚገድ አይሆንም። ይህ ደግሞ የግድ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቻ የሚጠበቅ ሳይሆን፣ ባደጉት ሀገራት እንደሚታየው ከወታደራዊ ማእከላትም ችግር ፈቺ ብቻ ሳይሆን፣ አለማችንን ካለችበት አንድና ሁለት እርምጃዎች ወደ ፊት የሚያስኬዱ የጥናትና ምርምር (በተለይም ቴክኖሎጂ በማመንጨቱ መስክ) ሲፈልቁ እየታየ ነውና ዘርፉ ብዙዎችን ያስተሳሰረና የሚያስተሳስርም ነው። ጉዳዩን እናቅርበውና ወደ ሀገራችን እናምጣው።

የእኛ ሀገር ምሁራን የጥናትና ምርምር ስራዎች በይዘትና አቀራረባቸው "አንቱ የተባሉ (ወይም፣ ሊባሉ የሚችሉ) ሆነው ሳለ እስከ ዛሬ ያተረፉት ግን መደርደሪያ ላይ እየተንቀዋለሉ አቧራ መቃም ብቻ ነው። እድሜያቸው እየጨመረ ሲሄድም በመጥረጊያ ተጠርጎ መጣል (በአሁኑ ዘመን አማርኛ መወገድ) ነው።

እኛ ሀገር ላይ ዋጋ ያጡት የጥናትና ምርምር ስራዎች ብቻ አይደሉም፤ እራሳቸው ተቋማት በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ያፈሰሱባቸውና ያስጠኗቸው ጥናቶች እንኳን ዞር ብሎ የሚያያቸው በመጥፋቱ በሁለትና ሶስት አመት ውስጥ እነዛው ጥናቶች እንደ ገና ብዙ ሚሊዮን ብር ተከፍሎ እንዲጠኑ ይደረጋል።

አይደለም የጥናትና ምርምር ስራዎች፣ የፖሊሲ ሰነዶች እንኳን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ የማይደረጉበት፣ ደንብና ሥርዓት እንደ ልብ የሚጣስበት፤ ስንትና ስንት ታሪካዊና ፍልስፍናዊ ድርሳናት ተሽቀንጥረው የሚጣሉበት የእኛ ሀገር ብቻ ሳይሆን፤ እንደ አህጉር በድፍን አፍሪካ የጥናትና ምርምር ስራዎች ስፍራ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ይህ ደግሞ ሀሚታ ወይም አሉባልታ ሳይሆን የአፍሪካ ህብረት ያዘጋጃቸውን የተለያዩ ሰነዶች በመመልከት የተደረሰበት ድምዳሜ ነው።

ሌላው ሀገር የሌሎች ሀገራትን የጥናትና ምርምር ስራዎች እየዘረፈ ወደ ራሱ በማዳቀልና ሥራ ላይ በማዋል ትርፋማ ሲሆን፤ ወደ አፍሪካ ሲመጣ ግን እውነቱ የተገላቢጦሽ ሆኖ ይገኛል። ከዚህም በማለፍ "ነጮቹ እኮ ከአፍሪካ የዘረፉትን ነው . . . በማለት ለመመፃደቅ ይሞከራል። ዝርዝሩ ብዙ ነው።



በፎረሙ ከሩሲያና አሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ተመራማሪዎች ታድመዋል፣

አሁን አሁን፣ የዓለም ሁለንተናዊ ግስጋሴ እየፈጠነና እየረቀቀ በመሄዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፤ አልያም በድሮው መንገድ የሚሄዱ በአዲስ መንገድ በሚሄዱት ሊሰለቀጡ የሚችሉበት እድልና አጋጣሚ እየገሰገሰ በመምጣት ላይ ሊሆን ይችላል አንዳንድ ሀገራት ወደ ቀልባቸው እየተመለሱ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም አንዷ ነች።

ዘንድሮ ከሌሎቹና ካለፉት ለየት የሚለው ምንጊዜም "ዩኒቨርሲቲዎች ከመማር ማስተማር ስራቸው በተጓዳኝ ችግር ፈቺ የምርምር ተግባራትን አጠናክረው ለሀገር እድገት የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ ማጎልበት እንዳለባቸው ሲናገር እንደ ነበረው፤ ሰሞኑንም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምርና ማህበረሰብ ጉድኝት ስራዎች ላይ የመከረውና በቦንጋ በተካሄደው የየዩኒቨርሲቲዎች ምክትል ፕሬዚዳንቶች ፎረም ላይም እንደደገመው፤ ትምህርት ሚኒስቴር ዘንድሮ ጉዳዩን በሕግ ማእቀፍ አስደግፎ፤ የሕግ ማእቀፍ እንዲኖረው አድርጎ ወደ ሥራ ለመግባት መንደርደሩ ነው። ወደ ሰነዶች እንሂድና ገዥ የሆነውን በመመልከት "አዋጁ ምን ይላል?የሚለውን እንይ።

ማንኛውም ተግባር በአግባቡ እንዲከናወን፣ የሚመለከታቸውም በራስ መተማመን መንፈስ ወደ ሥራ እንዲገቡ ከተፈለገ ጉዳዩ የሕግ ማእቀፍ ያስፈልገዋል የሚል ነገር አለ። እውነት ነው፤ አንድ ጉዳይ ወይም ተግባር የሕግ ማእቀፍ ካለው፣ የሕግ ማእቀፉ በአሰሪ ፖሊሲዎች ከተደገፈ ውጤታማነቱ የሚያሻማ አይሆንም።

ሰሞኑን ይፋ የሆነው፣ የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 የአዋጁን መውጣት አስፈላጊነት ሲያስቀምጥ፡–

- በሀገራችን የተጀመረውን ትምህርትና ሥልጠና ጥራትና ተገቢነት ማረጋገጥ ለምናስበው ሁለንተናዊ ብልጽግና ወሳኝ በመሆኑ፣
- የትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማረጋገጥ የተማሪዎችና ሠልጣኞች የተግባር ሥልጠና (ኢንተርንሽፕ)፣ የመምህራንና አሠልጣኞች የኢንዱስትሪ ተሞክሮና ጉድኝት (ኤክስተርንሽፕ)፣ የኢንዱስትሪ ሙያተኞች በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚያበረክቱት የተግባር ትምህርትና ሥልጠና አስፈላጊ በመሆኑ፣
- ከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና የምርምር ተቋማት ከኢንዱስትሪ ጋር በመተሳሰር ምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የማማከር አገልግሎት ሥራዎችን ማከናወን ስለሚጠበቅባቸው እና ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪ ለመገንባት ለኢንዱስትሪው ብቁ የሰው ኃይል፣ ችግር-ፈቺ ምርምር የማካሄድና ቴክኖሎጂ የማመንጨት ተልዕኮ ስላላቸው፣
- የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር በጋራ ተጠቃሚነትና የትስስር አካላትን ንቁ ተሳታፊነት ስለሚጠይቅ፤ እንዲሁም፣ በሀገራችን ብሔራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ላይ የተመላከቱ የትስስር ቁልፍ ጉዳዮችን በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፣
- በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) (፶፭(፩)) መሠረት የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ወጥቷል፡፡ በማለት ነው።

ከዚህ አኳያ ከተመለከትነው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከናወኑ የጥናትና ምርምር ስራዎች ለየአካባቢያቸው ማህበረሰብ ከሚሰጡት አገልግሎት ባለፈ አገራዊ ጥቅማቸው በቀላሉ የሚታይ አይሆንም ማለት ነው።

አዋጁ ትስስር (በፎረሙ ላይ "ጉድኝት በሚል ጥቅም ላይ ውሏል) የሚለውን መሰረተ ሀሳብ ሲያብራራም፡–

"ትስስር" ማለት በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ መካከል በዚህ አዋጅ በተደነገጉ አቅጣጫዎች፣ በጋራ ተጠቃሚነት መርሆዎች የሚካሄድ የተማሪዎችና ሠልጣኞች የተግባር ትምህርትና ሥልጠና (ኢንተርንሽፕ)፣ የመምህራንና አሠልጣኞች የኢንዱስትሪ ተሞክሮና ጉድኝት(ኤክስተርንሽፕ)፣ የኢንዱስትሪ ሙያተኞች በትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚያበረክቱት የተግባር ትምህርትና ሥልጠና፣ እና በትብብር የሚካሄድ የምርምር፣ ቴክኖሎጂ ሽግግርና የማማከር ሥራዎች ጉድኝት ሥራዎች ነው፡፡

**በማለት ሲሆን፤ ከፍተኛ የትምህርት ተቋምንም፡-**

"ከፍተኛ ትምህርት ተቋም" ማለት በመንግሥት ወይም በግል ባለቤትነት ሥር የሚተደደርና በተለያዩ የትምህርት መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የዲግሪ መርሐ ግብሮች የሚሰጥ፣ የጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ ጉድኝት ሥራዎችን የሚሠራ ተቋም ነው፡፡

በማለት ይገልፀዋል። የትስስሩ አካላትንም፡–

"የትስስሩ አካላት" ማለት የትስስሩ ዋና ተዋንያን ሲሆኑ እነርሱም ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው የኢኮኖሚ ሴክተር መሪ መሥሪያ ቤቶችና ተጠሪ ተቋማት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማት፣ የሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት፣ የግል አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች፣ የፌዴራልና ክልል ንግድ ምክር ቤትና ዘርፍ ማህበራት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ሀገር በቀል ድርጅቶች፣ የሙያና ሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች በምክር ቤቱ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ሲል ይዘረዝራል።

"የትስስሩ ዓላማን በተመለከተም– "የትስስር ሥራዎችን ሀገራዊ የልማት አጀንዳን ባገናዘበ መልኩ በቅንጅት፣ በወጥነት፣ በተጠያቂነት እና በብቃት በመተግበር፣ ውጤታማነትን፣ የጋራ ተጠቃሚነትን፣ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ ነው። ይላል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተግባር እና ኃላፊነትን በተመለከተም በአዋጁ አንቀፅ 9 ስር "የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነ[ቶች] ይኖ[ሩታ]ል በሚል ንኡስ ርእስ ስር የሰፈረ (ሰባት ነጥቦች) ሲሆን፣ ሙሉ ቃሉም የሚከተለው ነው።

በተቋማዊ የስትራቴጂ ሰነዶች ውስጥ የትስስር ሥራን የማካተት፤ የትስስር ሥራን ለመስራት የሚያስችል የሰው ኃይልና በጀት የመመደብ፣ የትስስር ገቢን የማስተዳደር እና የአሠራር ሥርዓት የመዘርጋት፤ በትስስሩ ሂደት የማህበረሰቡን ችግር ትኩረት ሰጥቶ መፍታትና ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ፤ በምክር ቤቱ የተለዩ እና ቅድሚያ የተሰጣቸውን የትስስር ተግባራት መሠረት በማድረግ የተቋሙን የተልዕኮ ልየታ ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ እንዲሁም፣ የቁልፍ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በሚያረጋግጥ አግባብ የማቀድና የመተግበር፤ በትስስር የሚከናወን ምርምርና ፈጠራ በትስስሩ ለማሳካት የተለዩትን የባለድርሻ አካላት ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን የማረጋገጥ እና አስፈላጊውን ፈንድ በጋራ ማፈላለግ፤ በትስስሩ የሚከናወኑ ተግባራት ለትምህርትና ምርምር ጥራት፣ ለማህበረሰብ ጉድኝት፣ ለኢንዱስትሪዎች እና ኢንተርፕራይዞች ውጤታማነት በሚያግዝ አግባብ መተግበሩን ማረጋገጥ፤ በትስስር የሚገኝ የአእምሯዊ ንብረት መብት ጸንተው ሥራ ላይ ባሉ ሕጎች እና የትስስሩን አካላት መብት እና ጥቅም በሚያስጠብቅ አግባብ ለትምህርታዊ አገልግሎቶች የማዋል ተግባርና ኃላፊነት አለበት፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች ልምድ ተለዋውጠውበታል፤ ቀጣይ የጋራ አቅጣጫ ተቀምጦበታል፤ አዳዲስ አሰራሮችና ፕሮግራሞች ተዋውቀውበታል፤ ከተለያዩ የመንግሥትና የግል ተቋማት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያስችል ስርአት ተዘርግቶበታል፤ እንዲሁም፣ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በተናጠል ከሚያደርጉት የጥናትና ምርምር ስራዎች ባለፈ በቅንጅት የሚሰሩበትን እድል ይፈጥራል፣ የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ ተደርጎበታል በተባለለት፣ በቦንጋ ዩኒቨርሲቲው የምክክር ፎረም ላይስ ምን ምን ጉዳዮች ተነሱ፤ ምን ውሳኔስ ተላለፈ?

የመንግሥትና የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተሳተፉበት፣ በተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ተግባራት አፈጻጸም ላይ በመከረው፤ ከሩሲያና አሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ተመራማሪዎች ጭምር በተገኙበት በዚሁ የምክክርና የጉድኝት መድረክ ላይ የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ጡሹኔ እንዳመለከቱት፣ ዩኒቨርሲቲዎች ከመማር ማስተማር ስራቸው ጎን ለጎን ችግር ፈቺ የሆኑ የተለያዩ ጥናትና ምርምር ስራዎችን በማከናወን ለሀገር እድገት የሚያደርጉትን አስተዋፅኦ አጠናክረው መቀጠል አለባቸው።

ከተቋቋመ ካለፉት 5 ዓመታት ጀምሮ በርካታ ተግባራትን ማከናወኑ፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በቴክኖሎጂ እንዲሁም በአካባቢ ጥበቃ መስኮች ያከናወናቸው ስራዎች ተጨባጭ ለውጥ ማምጣታቸው፣ አቅመ ደካማ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመለየት በየወሩ የገንዘብ ድጋፍ ከማድረግም ባለፈ፣ የመኖሪያ ቤትና የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታን በማከናወን ላይ መሆኑ በተነገረለት ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የተካሄደው ይህ ፎረም፣ በአይነቱ የመጀመሪያ ባይሆንም "የከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ የተዋወቀበትና የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለአገራዊ ፋይዳና ማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ለማዋል፤ ቃል የተገባበት መሆኑ "የመጀመሪያው ያደርገዋል።

በመጨረሻም፣ ምንም እንኳን "ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ስራዎች፣ "ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ . . .፣ "የአገሪቱን ልማት የሚያፋጥኑ፣ "የዲሞክራሲ ባህልን የሚያሰርፁ . . .፤ "ሰላምና ወንድማማችነትን የሚያሰፍኑ . . . ወዘተ የሚሉት የቃላት ድርድሮች እንኳን ለእኛ በሩቅ ለሚያውቁንም የሰለቹ ብቻ ሳይሆኑ የቸኮሉም ጭምር ናቸው። በመሆኑም፣ ሪፎርምን እጅጉን ይፈልጋሉ።

ምንም እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲን የመሳሰሉት የጥናትና ምርምር ስራዎችን እታች ድረስ በማውረድና አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ጥሩ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ ቢሆንም፤ እንደ ሀገር በዚህ መልኩ እየተሰራ ነው ለማለት ምንም አይነት ተጨባጭ ማስረጃ የለም። በመሆኑም፣ በዚህ፣ 5ኛ ትውልድ በሆነው ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ በተካሄደው ምክክር አማካኝነት ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውና ወደ ተግባር ለመግባት በአዋጅ የተደገፉት እቅዶች ያለ ምንም መዛነፍ ተጠናክረው ሊቀጥሉና ሙሉ ለሙሉ በተግባር ሊገለጡ፤ በተለይ፣ የምርምርና ማህበረሰብ ጉድኝት ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንቶችም ጉዳዩን ዳር ከማድረስ አኳያ በርትተው ሊሰሩ ይገባል እንላለን።

# “የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ሥርዓት የሚመራበት ሥርዓት በመስተካከሉ የነበሩት ችግሮች ተወግደዋል”

**አቶ ሰለሞን ገብሬ**
**የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ**


ፎቶ፦ ገበበ ገብሬ

**አስቴር ኤልያስ**

ባለፉት ጊዜያት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን በወቅቱ ለአርሶ አደሩ ለማድረስ ፈተና ሆኖ ሰንብቷል፡፡ ለፈተናው በዋና ምክንያትነት ሲጠቀስ የነበረው የውጭ ምንዛሬ እጥረት ቢሆንም ከእሱ ባልተናነሰ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ሥርዓቱም ማነቆ እንደነበር የዘርፉ አካላት ይጠቅሳሉ፡፡

ከዚህ አኳያ አርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩንና ሰፋፊ የመንግሥትና የግል እርሻ ባለቤቶችን የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓት እንዳይቸግራቸው ተቋሙ በአቅርቦቱም ሆነ በዋጋ መረጋጋቱ ላይ ምን እየሰራ ነው ሲል አዲስ ዘመን በግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ ከሆኑት ከአቶ ሰለሞን ገብሬ ጋር ቆይታ አድርጎ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍ በዋናነት እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት ምንድን ናቸው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፡፡ የተቋቋመውም የግብርና ሥራውን ለመደገፍ ነው፡፡ ዋና ተልዕኮው ለግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የግብርና ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደሩ ማቅረብ ነው፡፡

ይህ ተግባሩ ዘርዘር ተደርጎ ሲታይ ኮርፖሬሽኑ ምርጥ ዘር በማባዛት ለተለያዩ ስነ ምህዳር የሚውሉ ዘሮችን ያዘጋጃል፡፡ ከምርምር ተቋማት መነሻ ዘር ተቀብሎ በሶስት ደረጃ አባዝቶ ለአርሶ አደር ያደርሳል። ይህ ፕሪቤዚክ፣ ቤዚክና ሰርቲፋይድ ዘር በሚል አምርቶ በሀገሪቱ ላሉት የተለያየ ስነ ምህዳር ያቀርባል። እነዚህ ምርጥ ዘሮች በሽታን የመከላከል፣ ምርታማነት የመጨመር ብቃት ያላቸውና የተሻሻሉ ዝርያዎች ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የግብርና ግብዓት አቅርቦት ናቸው ከሚባሉት ውስጥ የአፈር ማዳበሪያ በጠጣርና በፈሳሽ ያቀርባል፡፡ ለሰብል እንክብካቤ የሚውሉ የተለያዩ አግሮኬሚካልስ ጸረ በሽታ፣ ጸረ አረም እንዲሁም ጸረ ተባይ በዚህ ልክ ከውጭ አስመጥቶ ያቀርባል። ሶስተኛው ደግሞ የእርሻ ሜካናይዜሽን አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የእርሻ ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሲባል ከማረስ ጀምሮ ጎተራ እስከማስገባት ድረስ እንደ ኮምባይነር ያሉ መሳሪያዎች አይነት አገልግሎት ነው። ማረስ ሲባልም ለአርሶ አደሩ በኪራይ የሚውል ሲሆን፣ ያርሳል፤ ይከሰክሳል፤ በሜካናይዜሽን ይዘራል፡፡ ከዚያ በኋላ እህሉ ሲደርስ አሁንም በኪራይ ከአጨዳው እስከ ጎተራ እስኪገባ አገልግሎቱ ለአርሶ አደሩ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ከኪራይ አገልግሎቱ ውጪ ደግሞ ግዥዎችን ያከናውናል፡፡ የእርሻ መሳሪያዎችን፣ ትራክተሮችን፣ ኮምባይነሮችን፣ ማረሻዎችን፣ መከስከሻዎችን እና መሰል መሳሪያዎችን ከውጭ በተመጣጣኝ ዋጋ ገዝቶ ለአርሶ አደሩ ያቀርባል፡፡

የውጭ ምንዛሬ ከማስገኘት አንጻር የእጣን ምርቶችን ከበረሃ አካባቢዎች አስለቅሞ በማምጣትና በማዘጋጀት ወደውጭ የመላክ ተግባር ያከናውናል። ከዚያ ውጭ ደግሞ የመለዋወጫዎች፣ ፓምፖችና የመሳሰሉትን ለአነስተኛ አርሶ አደሮች አገልግሎቱን ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ከባድ ተሽከርካሪዎችን በኪራይ ለውስጥ አገልግሎት ይሰጣል።

አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ የግብርና ግብዓት ከሚባሉት ውስጥ ዋናው የአፈር ማዳበሪያ ነውና በዚህ ረገድ ቀደም ሲል የተፈጠረው እጥረት መንስዔው ምን ነበር? ዘንድሮስ በምን መልኩ ለማስተካከል ተሰርቷል?

አቶ ሰለሞን፡- ኮርፖሬሽኑ በሀገሪቱ የአፈር ማዳበሪያ አቅራቢ ብቸኛ ኮርፖሬሽን ነው፡፡ አካሄዱም የአርሶ አደሩን የማዳበሪያ ፍላጎት ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ክልል ተጠናክሮ በግብርና ሚኒስቴር በኩል ፍላጎት ይመጣል፡፡ ግብርና ሚኒስቴር በዚያ ልክ በጀት ከገንዘብ ሚኒስቴርም ከብሔራዊ ባንክም አስይዞ በዛ መሰረት ግዢው ይከናወናል፡፡

ባለፈው ዓመት የተወሰነ ችግር እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ይኸው ከዚህ በፊት ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ላይ ሲውል የነበረ የግዥ ሥርዓት ነው፡፡ ያ ደግሞ አካሄዱ ውስብስ የሆነ ነው፡፡ ጨረታ መጠበቅ ግድ ይላል፡፡ ግልጽ ጨረታ መውጣት አለበት፤ አንዴ ውለታ ከታሰረ በኋላ ዋጋ እንኳ ቢቀንስ መቀነስ አይቻልም፡፡ የነበረው የግዥ ሥርዓት ግትር/አሳሪ ነበር፡፡ በመሆኑም ችግር ነበረበት፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን እሱን ችግር ለማስተካከል ጥረት በመደረጉ ሊያሰራ የሚችል የግዥ ሥርዓት መሆን ችሏል፡፡

ስለሆነም የዓለም ገበያ እየታየ ጨረታ መውጣት ካለበት ጨረታ ይወጣል፡፡ በውስን ጨረታ መሄድ ካለበትም በውስን ጨረታ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ የኮርፖሬሽኑ የሥራ አመራር ቦርድም ይህን በአግባቡ መምራት እንዲያስችል ሙሉ በሙሉ በአዲስ ተቀይሯል።

ይህንን ኮርፖሬሽኑን እንዲመሩ በቦርድ የተመደቡት የግብርና ሚኒስትር፣ የሎጂስቲክና ትራንስፖርት ሚኒስትር፣ የብሔራዊ ባንክ ገዥ፣ የንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት እንዲሁም የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የካቢኔ ኃላፊ ናቸው፡፡ ይህ የሆነው የባለፈው ዓመት ችግር እንዳይከሰት ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በተሳለጠ ሁኔታ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለአርሶ አደሩ በሰዓቱ እንዲቀርብለት ለማድረግ በመንግሥት በኩል ትኩረት ተሰጥቶት በመሰራት ላይ ነው፡፡ ይህም ለውጥ አምጥቷል፡፡

ከዚህ ቀደም የአፈር ማዳበሪያው ጨረታ ወጥቶለት ውጤት መጥቶ መርከቦቹ የሚደርሱት ታኅሣሥ ላይ ነው፡፡ አሁን ግን መንግሥት ልዩ ትኩረት በመስጠቱ የማዳበሪያ አሰራር ሥርዓትም በመሻሻሉ ከዚህ በፊት ተደርጎ በማይታወቅ ጥቅምት 18 ግዥው አልቆ ጂቡቲ ደርሷል፡፡ ይህ ለውጥ በተቀየረው የአሰራር ሥርዓት የመጣ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ለበልግ እና ለመስኖ የአፈር ማዳበሪያ ግዢው ተፈጽሞ ወደአርሶ አደሩ በፍጥነት መድረስ ችሏል፡፡ ድሮ ቢሆን በዚህ ሰዓት አንድም መርከብ ወደ ጂቡቲ ወደብ አይደርስም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ይህ ችግር ተፈትቷል፡፡ ምክንያቱም ውሳኔ ሰጪዎች ከፍተኛ ባለስልጣናት ናቸው፡፡ ግዥው ግልጸኝነት የተሞላው ነው፡፡ ዓለም አቀፉ ገበያ በሰፊው ይታያል፡፡

የዓለም አቀፍ ገበያ ከፍ ባለበት ጊዜ አንዴ ውል አስሮ የሚቀጥል አይደለም፡፡ ከዚህ በፊት ገበያውን የሚያጠኑ አጥኚዎችን አልቀጠርንም፡፡ አሁን ግን ዓለም አቀፍ ገበያውን የሚያጠኑ አጥኚዎች ተቀጥረዋል። የእነዚህ አጥኚዎች መረጃ ተይዞ ቦርዱ ያለው የግዥ ቴክኒካል ኮሚቴው ታክሎበት የሚሰራ በመሆኑ ችግሩ ሊፈታ ችሏል፡፡

ባለፈው ዓመት ችግሮች ነበሩ፡፡ ችግሩም በአሳሪ የግዥ ሥርዓት የተነሳ ነው፡፡ የኤልሲ ችግርም በስፋት የሚንጸባረቅ ነበር፡፡ በወቅቱ ንግድ ባንክ ቢጠየቅም የምንዛሬ ችግር እንዳለ አመልክቷል። አቅራቢዎቹ ደግሞ ከነበረው ሀገራዊ ሁኔታ አንጻር እያዩ ኤልሲው ይሁንታን ያገኘ መሆን አለበት ይላሉ፡፡ ያ ማለት ዋስትና ያለው ኤልሲ ማለት ነው፡፡ ያንን ደግሞ ዋስትና ያለውን በቀጥታ ለመክፈት ከነበረው ሁኔታ አንጻር ባንኮች ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ አቅራቢዎቹ ኤልሲ የተረጋገጠ ካልሆነ ሽያጩን ማከናወን አይችልም የሚል ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ በመሃል ወደሁለት ወር አካባቢ በመዘግየቱ ኤልሲ መክፈት አልተቻለም፡፡ እሱ ደግሞ የፈጠረው ክፍተት ከእቅድ ውጪ መሄድን ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ይህንን እጥረት በመጠቀም አርሶ አደሩ ዘንድ የተለያየ ተገቢ ያልሆነ መረጃ መናፈስ ጀመረ፡፡

ነጋዴዎች እጥረት ባለበት አካባቢ ስለሚመጡ ወደዚያ የማምራት ሁኔታዎች መጡ፡፡ በአማራ ክልልም ተፈጥሮ የነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋት እና የመሳሰሉ ነገሮች ተደራርበው ባለፈው ዓመት ችግር እንዲፈጥር አድርገው ነበር፡፡ በአሁኑ ውቅት ግን መንግሥት ያንን ችግር በማየት ችግሩ እንዳይደገም በማድረጉ አሁን በተሳለጠና በተሳካ ሁኔታ ግዥዎች ተከናውነው በሰዓቱ ለበልግና ለመስኖ ለአርሶ አደሩ በበቂ ሁኔታ እና በጊዜ እየደረሰ ይገኛል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ችግር ሲፍጥር የነበረው የማዳበሪያ ግዥ ሥርዓቱ ችግር ስላለበት ነው ተብሏል፤ ችግሩ ከዚህ በኋላ የማያዳግም ችግር ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አዎ! የግዥው መመሪያ የተዘጋጀው በግብርና ሚኒስቴር እና በገንዘብ ሚኒስቴር ነው። መመሪያውን መንግሥት ከላይ ክትትል በማድረግ ማነቆው መፈታት አለበት በሚል ከሀገሪቱ አጠቃላይ የግዥ ሥርዓት የተሻሻለ እና የተለየ፣ እንደየሁኔታው ተለዋዋጭ የሆነ የማዳበሪያ እጥረት ሊያጋጥም በማይችል መልኩ ይፈታል ተብሎ ታስቦ የተዘጋጀና ራሱን የቻለ መመሪያ አለ፡፡ መመሪያው በገንዘብ ሚኒስቴር ጸድቆ ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኳል። ስለዚህ የተሰራው ሥራ የማያዳግም ነው ማለት ይቻላል፡፡

የክልሎችን፣ የገንዘብ ሚኒስቴርን፣ በማዳበሪያ ግዥ ላይ ያሉ ሁሉ ተዋናይ ኃላፊነታቸውን፣ መብታቸውን፣ ግዴታቸውን የጠቀሰ ነው፡፡ ጸድቆ በሥራ ላይ ስለዋለ በገንዘብ ደረጃ ብዙ ለውጥ አምጥቷል፡፡

ለአብነት ያህል በባለፈው ዓመት የነበረው አሰራር አንድ ጊዜ በዚህ ወቅት ጨረታ አውጥተን ጥቅምትና ኅዳር አካባቢ የነበረን ዋጋ ወስነን እንይዛለን፡፡ የአፈር ማዳበሪያው ኅዳር ላይ ሊቀንስ ይችላል፡፡ በተለይ ዩሪያ የሚባለው ዋጋው በጣም ተለዋዋጭ ነው፤ አንዴ ከፍ፤ አንዴ ደግሞ ዝቅ ይላል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ እንደ ሕንድ፣ ፓኪስታን፣ ብራዚል ያሉ ሀገራት በሚያወጡበት ሰዓት እኛ እንዳጋጣሚ ሆኖ እዛ ውስጥ ልንገባ እንችላለን፡፡ በዚያን ሰዓት የሰጡንን ከፍተኛ ዋጋ ይዘን እንቀመጣለን፡፡

የቀደመው ግዥ አሰራር አንዴ ውለታ ከተገባ በመንግሥት ግዥ ባለስልጣን ተነጋግሮ ለማስቀነስ ፈቃድ ተጠይቆ ነው፡፡ እንደዚያ አይነት አሰራር ደግሞ የሚያመጣው ሙስናንም ጭምር ነው፡፡ አንዴ ውል ከተገባ ቢጨምርም መቀነስ አይቻልም፡፡ ቢቀንስም ደግሞ እንደዚያው ነው፡፡ እንዲያውም ብዙ ጊዜ የሚያጋጥመን ፈተና አቅራቢዎቹ መሸሻቸው ነው። ሲጨምር “ማቅረብ አንችልም” በሚል ኮንትራቱ የሚፈርስበት እድልም አለ፡፡ እኛ ደግሞ በመንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር መመሪያ ስለምንመራ እናስቀንስ ሲባል አይፈቀድም፡፡

በአሁኑ ወቅት ግን በመመሪያው የምንፈልገው መጠን ዓለም አቀፍ ገበያውን እያየን በተለየ ሁኔታ በቦርዱ ውስጥ ያለው የአመራሩ ስብጥርም የዓለም አቀፍ ገበያው እውቀቱ ያላቸው እንደመሆናቸው በዛ ልክ ተረድተው “በዚህ ጊዜ ጨረታው ይውጣ፤ ይህንን አሁን እንግዛ፤ በቀጣይ ደግሞ እንዲህ እናድርግ፤” የሚሉ በመሆናቸው መርህ ግብር ወጥቶለት እየተሰራ ነው፡፡ ስለሆነም አካሄዱ መልካም የሚባል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለ2016/17 የምርት ዘመን እንዳለፈው ጊዜ የአፈር ማዳበሪያ ችግር እንደማይኖር ተጠቅሷል፤ በዚህ ዓመት በእቅድ ደረጃ የተያዘው ምን ያህል ነው?**

**ወደ ገጽ 10 ዞሯል**

# “የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ሥርዓት...

ከ ገጽ 9 የዞረ



**አቶ ሰለሞን፡-** በዚህ ዓመት እንደ እቅድ የተያዘው የአፈር ማዳበሪያ ሁለት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ነው፡፡ ኤንፒኤስ ወደ 332 ሺ ቶን፣ ኤንፒኤስ ቢ ወደ አንድ ሚሊዮን ቶን፣ ሲሆን፣ ዩሪያም ተጠቃሽ ነው። መንግሥት በፈቀደው የውጭ ምንዛሬ የሚገዛ ነው፡፡

ነገር ግን የተፈቀደለት እቅድ የያዝነው አንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ቶን ነው፡፡ ይህ መርሀ ግብር ወጥቶለታል። አሁን ያሉት የቦርድ አመራር በእውቀትም ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያም የተለዩ ናቸው፡፡ ግብርና ሚኒስቴር መቼ? ምን? መገዛት አለበት የሚለውን አቅርቧል፡፡ ለመኸር ይህን ያህል፣ ለመስኖና ለበልግም ይህን ያህል ተብሎ ተቀምጧል። በዛ መሰረት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም የባለፈው አይነት ችግር እንዳይፈጠር የባንኩ ፕሬዚዳንት አብረውን ናቸው፡፡ የምንዛሬ ችግር ከተባለ እንኳ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥው የቦርድ አባል በመሆናቸው የሚሰራው በመናበብ ነው፡፡ ከጸጥታም ሆነ ከሌላ ችግር አንጻር እንኳ ችግር እንዳያጋጥም የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ኃላፊ እንዲሁ በቦርዱ የተካተቱ ናቸው፡፡ የትራንስፖርት ችግር አለ ቢባል እንኳ ሚኒስትሩ የዚሁ የቦርድ አባል ናቸው። ከዚህ አኳያ ችግሩ የማያዳግም እንዲሆን ተብሎ መንግሥት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

ስለዚህ ለበልግና ለመስኖ በቂ ግብዓት ለአርሶ አደሩ እየደረሰ ነው፤ ምናልባት አማራ ክልል ባጋጠመው የጸጥታ ችግር በተወሰነ መልኩ ችግር ብለን የምንለው ተሽከርካሪዎች በአጀብ እየሄዱ መሆኑን እና አሽከርካሪዎች ደግሞ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ስጋት ብጤ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ ከዛ ውጪ በአሁኑ ወቅት በታቀደው መጠን እየተሰራበት ነው፡፡

የኤንፒኤስ ዝርያ የሚባሉት 60 በመቶ የአፈር ማዳበሪያ ድርሻ የሚይዙት ውለታው ተፈርሞ ግዥው ተከናውኗል፡፡ አሁን በወጣለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ኤልሲዎች እየተከፈቱ መርከብ ይዞት ይመጣል፡፡ ከዚያም ወደየአርሶ አደሩ ይደርሳል፡፡ ዩሪያን ስንወስድ አቅራቢዎቹም የተበጣጠሱ ናቸው፡፡ ዋጋ ዓለም አቀፍ ገበያ ላይ በጣም ተለዋዋጭ ነው፡፡ ዛሬ ርካሽ ነው ሲባል ነገ የሚወደድበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ ዩሪያን በብዛት የሚጠቀሙ አገሮች አሉ፤ ከእነዚህም ውስጥ ሕንድ፣ ቻይና እና ብራዚል ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ቻይና ለራሷ ሲያንሳት ወደውጭ የምትልከውን ማዳበሪያ ትጠቀማለች፡፡ በዚያን ወቅት በዓለም አቀፉ ገበያ ላይ እጥረት ይፈጠራል። በሌላ መልኩ ሕንድ ገበያ ላይ ስትወጣ ከፍተኛ ግዥ ትፈጽማለች፡፡ በዚያን ጊዜ አቅራቢዎች የሚሄዱት ወደ ሕንድ ነው፡፡ በዚያን ወቅት ዋጋው ከፍ ይላል፡፡

ስለዚህ አሁን በመንግሥት የአሰራር ለውጥ በመደረጉ እንደገበያው ሁኔታ ተለዋዋጭ ሆነን መግዛት እንድንችል አድርጎናል፡፡ ዋጋው ውድ ከሆነ አንገዛም፡፡ ርካሽ ከሆነ ደግሞ እንገዛና ይዘነው እንቆያለን፡፡ ስለዚህ ከገበያው ባህሪ ጋር እንድንሰራ አድርጎናል፡፡ የበፊቱ የግዥ ሥርዓት ሆኖ ቢሆን ኖሮ ግትር በመሆኑ ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡ አንዴ ከተዋዋልን ተዋዋልን ማለት ነው፤ መቀየር አያቻልም። እንቀንስ ለማለም ጭንቅ ነው።

እንዲያውም የአሁኑ የኢፌዴሪ የግብርና ሚኒስትር ወደ ሚኒስትርነት ከመጡ በኋላ እንደምንም ብለው ያስቀነሱበት ሁኔታ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ የበለጠ ለውጥ መምጣት ስለቻለ ጥሩ ሒደት ላይ ነው ያለው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ለበልግና መስኖ የሚያስፈልግ የአፈር ማዳበሪያ ወደአርሶ አደሩ በምን መልኩ እየተሰራጨ ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ለበልግም ለመስኖም የተያዘው መጠን ሙሉ በሙሉ ግዢው ተከናውኗል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አማራ አካባቢ ካለው የጸጥታ ችግር ባሻገር 80 እና 90 በመቶ ወደ አርሶ አደሩ ሄዷል፡፡ ጂቡቲ ላይ ያለው የማጓጓዝ ሥራ ካልሆነ በስተቀር ሙሉ ለሙሉ ግዥ ተፈጽሟል፡፡ ይህም ከመጣ በኋላ የበልግም የመስኖም ማዳበሪያ ወደ ዩኒየኖችና አርሶ አደሮች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከመኸሩስ ጋር በተያያዘ ከወዲሁ ምን እየታሰበ ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** የመኸሩ ገና ነው፤ አስቀድሜ እንዳልኩት 60 በመቶ የሚይዘው ኤንፒስ ግዥው ተከናውኗል፡፡ ይህ ማለት ለሶስቱም የምርት ወቅቶች ማለትም ለበልግ፣ ለመስኖ እና ለመኸር ውለታው ተገብቶ ግዢው ተፈጽሟል፡፡ ችግሩ ታድያ ምንድን ነው? ከተባለ በአሁኑ ወቅት አምጥተነው ማከማቻ ማቆየት አንችልም። ከአቅራቢው ጋር ውለታ ተፈራርመናል። አስቀድሜ እንደጠቀስኩት ለመስኖም ለበልግም መጥቷል፡፡ ይህንንም ለአርሶ አደሩ አድርሰናል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለበልግና ለመስኖ እንጂ ለመኸር ጊዜው ገና ስለሆነ ይህ እንዳለቀ ሄዶ ማምጣት ብቻ ነው፡፡ የመጣውን ደግሞ በሰዓቱ እናደርሳለን፡፡

ውለታ ያልፈጸምነው የዩሪያን ነው፤ የቀረው የመኸር ነው፡፡ የመኸሩን ያልፈጸምንበት ምክንያት ደግሞ እንደድሮ ግትር የሆነ አተያይ ስለሌለን ነው፡፡ አስቀድመን ገበያውን እናጠናለን፡፡ ገበያ ላይ ዛሬ ውድ ሊሆን ይችላል፡፡ ውድ ከሆነ ደግሞ እኛ አንገዛውም። እንጠብቅና ርካሽ የሚሆንበትን ጊዜ አይተን ወቅቱ ከመድረሱ በፊት ግዥውን ፈጽመን እንደርሳለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አንዱ ተልዕኳችሁ የግብርና ግብዓቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶ አደሩና ለከፊል አርብቶ አደሩ ማቅረብ እንደመሆኑ በማቅረቡ በኩል የደላላን ጣልቃ ገብነት የምትከላከሉት እንዴት ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** የግብርና ስራዎች ግዥ የሚከናወነው በግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን ነው፡፡ የተወሰነ ከአጠቃላይ ግዥው ደግሞ ከአምስት በመቶ ያልበለጠ እና ከዛ በታች በሆነ መንገድ የማሰራጨት ስራም ይሰራል፡፡ ይህ ማለት 95 በመቶው ወደ ክልሎች ቀጥታ የሚሄደው ከጂቡቲ ነው፡፡ በመጀመሪያም ቢሆን ፍላጎቱ የሚነሳው ከክልሎች ነው፡፡ ይህም ከቀበሌ ጀምሮ ነው፡፡ እሱ ፍላጎት ተጠናቅሮ በግብርና ሚኒስቴር በኩል ግዥው እንዲፈጸም ወደእኛ ዘንድ ይመጣል፡፡

እኛ ግዥውን እንዳከናወንን የባህር ትራንስፖርትና የሎጂስቲክ አገልግሎት መርከብ ተከራይቶም ሆነ የራሱ መርከብም ካለው ከመጫኛ ወደብ ይዞት ይመጣል፡፡ ከዚያም ጂቡቲ ያራግፋልና መኪና አዘጋጅቶ ወደዩኒየኖች ያደርሳል፡፡ ይህ ማለት 95 በመቶ እና ከዚያም በላይ ማለት ነው፡፡

እንደጠቀስኩት አምስት በመቶ እና ከዚያ በታች የሆነችውን እኛ መጋዘን ይገባል፡፡ ያኛው 95 በመቶው ያልኩሽ ቀጥታ ለአርሶ አደሩ የሚሰጥ ነው። የግል ኢንቨስተሮች፣ ሰፋፊ ባለእርሻዎችና የምርጥ ዘር አባዥ ድርጅቶች የሚገዙት ከእኛ ነው፡፡ ይህንንም ቢሆን የምንሸጠው እኛ አይደለንም፡፡ ኢንቨስተሩ ቀጥታ ለግብርና ሚኒስቴር፣ ክልል ላይ ያለ ኢንቨስተር ከሆነ ደግሞ ክልሉ መረጃውን ገልጾ ለግብርና ሚኒስቴር ይልካል፡፡ ግብርና ሚኒስቴሩ ሳይፈቅድ እኛ አንዲት ፍሬ መሸጥ አንችልም፡፡ ለግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን “እከሌ የሚባል የእርሻ ባለቤት ወይም እከሌ የሚባል የምርጥ ዘር ድርጅት ይህን ያህል ሔክታር መሬት በዚህ ክልል ስር ስላለውና ክልሉም ስለደገፈው ከእናንተ ይህን ያህል የአፈር ማዳበሪያ እንዲገዛ ተፈቅዷልና ሽጡለት” ይላል፡፡ እኛ በዛ መልኩ ሽያጩን እናከናውናለን። በዚህ መልኩ ክልል አረጋግጦ ለግብርና ሚኒስቴር ልኮ ግብርና ሚኒስቴር ደግሞ ይሸጥለት ሲል በትእዛዙ መሰረት ሽያጮችን እናከናውናለን፡፡

በዚህ መሃል ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ማዳበሪያ ወዳልተፈለገ ቦታ ሊሄድ አይችልም ወይ? ከተባለ አይታወቅም ሊሄድ ይችላል፡፡ የእኛ ኃላፊነት ግን ሽያጭ ማከናወን ነው፡፡ ነገር ግን ክልሉ ያስፈቀደለትን እና የደገፈውን ድርጅት እዛ ድረስ መምጣቱን መከታተል ይፈልጋል፡፡

ክልሉ ለግብርና ሚኒስቴር የሚልከው ሰነድ “ለእከሌ ድርጅት ማዳበሪያ ይሰጥልኝ፤ እደግፋለሁ፤ እኔ ዘንድ ኢንቨስተር ነው” ብሎ ነው፡፡ ግብርና ሚኒስቴርም ወደእኛ ዘንድ ይልከዋል፡፡ ግልባጭ ላይ የሚደረገው ማዳበሪያው ክልል መድረሱንና ለተፈለገው መዋሉን ክትትል ያድርግ ይላሉ፡፡ ስለዚህ የእኛ ሚና እዚህ መስጠት እንጂ ክልል ላይ ሔዶ መከታተል አይደለም። በዚህ አጋጣሚ ግን ሕገ ወጦችን በምናይበትና በምናገኝበት ጊዜ የበኩላችንን ለመከላከል ጥረት እናደርጋለን፡፡ ለምሳሌ እንደ ሀገሪቱ ስንመለከት አንድ ሚሊዮን 940 ሺ ሜትሪክ ቶን ማዳበሪያ ተገዝቷል፡፡ የዚህ 90 በመቶ ቀጥታ የሚሄደው ክልሎች ዘንድ ነው።

እኛ በቅርቡ ያደረግነው ነገር ቢኖር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ፈጥረን መረዳቱ እንዲኖር ነው። በተለይ ችግር ሲኖር መከላከል እንዲቻልና የአሰራር ሥርዓት መለወጡን እንዲሁም ማዳበሪያው በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚመጣ መሆኑን ግንዛቤ እንዲኖር ነው። መንግሥት የአሰራር ለውጥ ስላመጣ እነርሱም በዚያው ልክ እንዲረዱ ባለድርሻ አካላትን አወያይተናል።

በእርግጥ በማዳበሪያ ዙሪያ እጥረት ሲኖር ሕገ ወጦችም አብረው ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ ከዚህ ጋር ተያይዞ አሽከርካሪዎች ጭምር ክትትል ይደረግባቸዋል። በተለይ ከጂቡቲ ጭነው ሲወጡ አራት ቦታ ክትትል የሚደረግባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ አጉድሎ የመጣ ትራንስፖርት ሰጪ በወንጀል እንዲጠየቅ ይደረጋል። የሚከፍለው ደግሞ እኛ በገዛንበትና ለአርሶ አደሩ በሚደርሰው ዋጋ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ትራንስፖርት ሰጪ ድርጅት ቀደም ሲል ሲያደርግ የሚስተዋለው ማዳበሪያውን ገበያ ላይ ወስዶ በውድ ዋጋ ይሸጠውና “ጎደለብኝ ልክፈል” ይል ነበር። እሱ ግን አሁን አይሰራም፡፡ ድሮ ጉድለት ሲኖር ራሱ የጉድለት ማስከፈያ ሥርዓት አለ፤ የመበላሸት፣ የመገልበጥና በተለያየ ምክንየያት የሚመጡ ጉድለቶችን ያን ያህል ሕገ ወጥ የሆነ ስላልነበር በዛ መልኩ ይሰራ ነበር፡፡ አሁን ግን የሚያስጠይቀው በወንጀል ነው። ከፍሎ ብቻ መገላገል የሚባል ነገር የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ማኅበሩን እስከማገድና ተጠያቂ እስከማድረግ የሚያደርስ ሲሆን፣ ይህ ሹፌሩንም የሚጨምር ነው። በአሁኑ ወቅት ግን በተለይ በዚህ ዓመት አቅርቦቱም አስተማማኝ ሲሆን፣ ስራውም የተሳለጠ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እስካሁን ባለው አካሔድ የታየው ነገር ቢኖር ስኬታማነቱ ነው፡፡ በተለይ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ስርዓት ከግትር ባህሪው ተላቅቆ እንደየግዥ ባህሪው ሊለዋወጥ ስለሚችል ችግሩ ተወግዷል፡፡ ትንሽ ችግር ያለው ዩሪያ ላይ ነው፡፡ የበልግና የመስኖው እንዳልኩት ሙሉ በሙሉ የቀረበ ሲሆን የቀረን ጥቂት የበልግ ነው፤ እሱም በትክክለኛው ሰዓት የሚቀርብ ይሆናል፡፡ ትንሽ በቀይ ባህር አካባቢ እንደ ስጋት ከሰሞኑን የታዩ ነገሮች አሉ፡፡ ይህ ደግሞ ዓለም አቀፍ ችግር ነው፡፡ ምናልባት እንደስጋት ልናይ የምንችለው እሱን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ ከምርምር ተቋማት መነሻ ዘር ተቀብሎ እንደሚያባዛና ለተለያዩ ስነ ምህዳር እንዲውሉ ማድረግ ላይ ይሰራል፤ ከዚህ አኳያ የተከናወኑ ተግባራት እንዴት ይገለጻሉ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ኮርፖሬሽኑ ሲመሰረት የተለያዩ አምስት ድርጅት ተዋህደው ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ምርጥ ዘር ድርጅት፣ የእርሻ መካናይዜሽን አገልግሎት፣ የግብርና ግብዓት አቅርቦት ዘርፍና ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመው ከ2008 ዓ.ም ነው። ከዛ በፊት ግን ለሀገሪቱ ብቻውን ምርጥ ዘር አቅራቢ የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት ነው፡፡ ኮርፖሬሽኑም የምርጥ ዘር ክፍተቶችን እየሸፈነ ከመሆኑም በተጨማሪ በራሱ ደግሞ አዳዲስ የሚላቸውን እያስመጣ እና እያባዛ ነው፡፡ የአቅሙን ያህል እያደረገ ነው፡፡

በመካናይዜሽኑም በኩል ያለው ከመካናይዜሽን አገልግሎት ጋር ከመዋሃዳችን በፊት ልክ እንደ ምርጥ ዘሩ መካናይዜሽንም ለብቻው በራሱ ይሰራ የነበረ ነው፡፡ የመካናይዜሽን አገልግሎት ቀደም ሲል ማረስ፣ መከስከስና ምርት እስከመሰብሰብ ድረስ ያለውን ይሰራ ነበር፡፡ ወደ እኛ በሚመጣበት ጊዜ አቅሙ ያን ያህል ከፍተኛ አልነበረም፡፡ ወደ እኛ የመጣው ተዳክሞ ነው።

ከዛ በኋላ ግን አዳዲስ ትራክተሮችን፣ ኮምባይነሮችን ተቀጽላ ማሽነሪዎችን አገልግሎት በመስጠትም ተደራሽም በመሆን ላይ ነው፡፡ የገበያ ክፍተት አለባቸው ወደሚባሉ ክልሎች ዘንድ እየሄደ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል። ይሁንና ውስንነት መኖሩ የሚካድ አይደለም፡፡ ነገር ግን ኮርፖሬሽኑ በተሰጠው ካፒታል መጠን ባሉት ትራክተሮችና ኮምባይነሮች አገልግሎቱን በመስጠት ላይ ነው፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን የእርሻ መሳሪያ የሚሆኑ መለዋወጫዎችን እየገዛን እናቀርባለን፡፡ ይሁንና አሁን ላይ የውጭ ምንዛሬ እጥረቱ አለ፡፡ ቢሆንም የአማራ ክልል የውጭ ምንዛሬ አግኝቶ ስለነበር ከ80 ትራክተሮች በላይ ገዝተን አስረክበናቸዋል። እኛም በራሳችን የምናመጣቸውን ለሚፈልጉ ክልሎች እንዲሁም ለባለሀብቶች የእርሻ መሳሪያውን ብቻ ሳይሆን አብሮ ተቀጽላ መሳሪያዎችን እያመጣን እንሸጣለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ እናመሰግናለን።**

**አቶ ሰለሞን፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የልባሽ ጨርቆች ገበያ መድራት - የአልባሳት ኢንዱስትሪው ስጋት

**ሰሚራ በርሀ**

በኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት ሲሰራ ቆይቷል፤ በእዚህም በተለይ የውጭ ምንዛሬ ሊያስገኙ ለሚችሉ የጨርቃ ጨርቃ ኢንዱስትሪዎች ትኩረት መሰጠቱ ይታወቃል። ዓለም አቀፍ ብራንድ ያላቸው የውጭ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው አልባሳትን በማምረት ለውጭ ገበያ እያቀረቡም ይገኛሉ፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ በተለይ በባህል አልባሳት ማምረት በኩልም እየተሰራ ነው፡፡ ይህን ተከትሎም በባህል አልባሳት ማምረት ሥራና አልባሳቱን ሸምቶ በመጠቀም በኩል ለውጦች እየመጡ ስለመሆናቸው በዘርፉ የተሰማሩ ዲዛይነሮች፣ አምራቾችና ነጋዴዎች ሲገልጹም ይደመጣል።

በአንጻሩ ከውጭ ሀገሮች የሚመጡ ልባሽ ጨርቆች በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በግልጽ ሳይቀር እየተቸበቸቡ ይገኛሉ፡፡ የቦንዳ ቤቶች መስፋፋትም ልባሽ ጨርቆቹ በስፋት ገበያ ላይ እየዋሉ መሆናቸውን ይጠቁማል፡፡

እነዚህ በምእራባውያን ሀገራት ጥቅም ላይ ውለው በበርካታ የአፍሪካ ሀገሮች ገበያዎች የሚሰራጩ ልባሾች (በተለምዶ ሰልባጅ እየተባሉ የሚጠሩት) በኢትዮጵያም በስፋት መሰራጨታቸው ለሀገር ውስጥ የአልባሳት ምርት ገበያ ስጋት ሊሆኑ እንደሚችሉ እየተጠቆመ ይገኛል፡፡

የእነዚህ በተለያዩ መንገዶች ወደ ሀገሪቱ የሚገቡ አልባሳት ግብይት እንደ አዋጭ የሥራና የገበያ አማራጭ እየታየ መጥቷል፡፡ ይህ ሁኔታ ለሀገር ውስጥ አልባሳት አምራቾችንና በጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን እንቅስቃሴ ፈታኝ ሊያደርግ እንደሚችል እየተጠቆመ ነው፡፡

በእነዚህ ልባሽ ጨርቆች ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ኢንስቲትዩት መምህር እስጢፋኖስ ምንቻግሮት፤ የልባሽ ጨርቆች ጉዳይ ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት አጀንዳ ሆኖ በስፋት እየተዘዋወረ እንደሚገኝ ያስረዳሉ፡፡ የጉዳዩን ተጽዕኖ በሁለት መልኩ ማየት እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል፡፡

በአንዳንድ ሀገሮች የልባሽ ጨርቆችን መጠቀም የዘመናዊነት መገለጫ ተደርጎ እንደሚወሰድ ጥናቶች እንደሚያመላክቱ መምህሩ ጠቅሰው፣ ለዚህ እንደ ምክንያትነት የሚጠቀሰውም «አልባሳቱ አዲስ ልብስ ተመርቶ ለገበያ እስኪቀርብ ድረስ ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶች ያስቀራል» የሚለው መሆኑን ይገልጻሉ፤ በድጋሚ ጥቅም ላይ ሲውሉ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ይቀንሳሉ የሚል እሳቤ እንዳለም ይናገራሉ።

በሌላ በኩል የልባሽ ጨርቆች ገበያው ለበርካታ ሰዎች የሥራ እድል መፍጠር ችሏል ቢባልም፣ ከጉዳቱ ጥቅሙ ያመዝናል በሚል የሚሞግቱ እንዳሉም ይናገራሉ። እነዚህ የልባሽ ጨርቆች ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ የማያደርጉና፣ የሚፈጥሩትም የሥራ እድል በዘርፉ የተሰማሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሚፈጥሩት የሥራ እድል ጋር የሚነጻጸር አይደለም የሚል ሀሳብ በማቅረብ የሚከራከሩም እንዳሉም ይገልጻሉ።

የልባሽ ጨርቆች ተጠቃሚነት በአፍሪካ እጅግ በጣም የበዛ መሆኑንም ጠቅሰው፣ አህጉሩ የምዕራባውያን የማይፈለጉ ምርቶች ማስወገጃ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ከጊዜ ወደጊዜ ቁጥሩ ሲጨምር ከኢኮኖሚያዊ ጫናው በዘለለ ማህበራዊ ጫናው እንደሚበልጥም ነው ያስገነዘቡት፡፡

«በሀገራችን የልባሽ ጨርቆች መበራከት በአልባሳት ኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እንደዚሁ በቀላሉ የሚተው አይደለም» የሚሉት መምህሩ፤ ተቀባይነቱ በጨመረ ቁጥር በሀገራችን ኢንዱስትሪውን ለማሳደግ እየተሰራበት ያለውን እንቅስቃሴ እንደሚያቀጭጭ ይናገራሉ። በሥራ ላይ ያሉ ፋብሪካዎችንም ጭምር ሙሉ ለሙሉ ከገበያው ሊያስወጣ እንደሚችልም ያስረዳሉ፡፡

ሰዎች ልባሽ ጨርቆችን ሲያስቡ ለየት ያሉ ልብሶች መሆናቸውን ፣ በጣም በቅናሽ ዋጋ መቅረባቸውን ሊያስቡ ይችላሉ፤ ጥራታቸውን የጠበቁ የሚሉ ጉዳዮች ቀድሞ ወደአዕምሯቸው ሊመጣ ይችላል የሚሉት መምህር እስጢፋኖስ፣ ይህ አዕምሮን የተቆጣጠረ ነገር በሀገር ውስጥ ለሚመረቱ ልብሶች ያለውን አመለካከት ይቀይረዋል ይላሉ፡፡ የሀገር ውስጥ ምርቶች ጥራት የወረደ ነው የሚል እሳቤን እንደሚፈጥርም ጠቅሰው፣ ይህ እሳቤ እየተቆጣጠረን ሲሄድ ፍጹም ጥገኛ የሆነ አመለካከት ያለው ማህበረሰብ እንዲፈጠር ያደርጋል ሲሉም ያስገነዝባሉ፡፡

የአልባሳት ኢንዱስትሪው ልብስ በማምረት ሂደት ውስጥ ከሚፈጠረው የሥራ እድል ባሻገር ለማምረት የሚረዱ ግብዓት አቅራቢዎችንም ጨምሮ ረጅም የገበያ ሰንሰለት እንዳለው የሚገልፁት መምህሩ፤ የዘርፉ ማደግ የሀገር ውስጥ አምራቾችን ከማበረታታት ባሻገር ዜጎች ባህላቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ይናገራሉ፡፡

እንደ መምህሩ ማብራሪያ፤ የልባሽ ጨርቆች ገበያው ውስጥ መበራከት የሀገር ውስጥ አልባሳት አምራቾች በኢንዱስትሪው ውስጥ ጸንተው እንዳይቆዩ በገበያው ላይ ተቀባይነት አግኝተው ደንበኞችን እንዳያፈሩ ያደርጋል፤ በልባሹና በሀገር ውስጥ በሚመረቱት አልባሳት መካከል ያለው የዋጋ ልዩነት የሀገር ውስጥ ምርቶችን ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡ በተለይ በማምረት ሂደትም የሚያወጡት ወጪ ከፍተኛ በመሆኑ አምራቾች ዘንድ ተጨማሪ ፈተና ነው ፡፡

በተጠቃሚዎች ዘንድ የቦንዳ ልብሶች ጥራት አላቸው የሚል እሳቤ እንዳለም ጠቅሰው፣ የሀገር ውስጥ ባለሙያዎች በጥራት የተሻሉ ልብሶች የማምረት ደረጃ ላይ ሊደርሱ እንደሚችሉ መታወቅ እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡ አንዳንድ አምራቾችም የሚያመርቷቸውን ጥራት ያላቸው ልብሶች ለውጭ ገበያ ብቻ የሚያቀርቡ መሆናቸውም የኢንዱስትሪው ክፍተት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

የልባሽ ጨርቅን ታንዛኒያ፣ ሩዋንዳ ፣ ዚምቡዋቤ እና ኡጋንዳ ወደ ሀገራቸው እንዳይገባ በተለያየ ጊዜ አግደዋል ያሉት መምህር እስጢፋኖስ፤ ሀገራቱ ይህንን ሕግ በማውጣታቸውም የተለያዩ ጫናዎች እንደደረሰባቸውም ጠቁመዋል፡፡ ለእዚህም ምክንያቱም በዚህ ገበያ ቀላል የማይባል ገንዘብ ይዘዋወራል፡፡

በኢትዮጵያም የልባሽ ጨርቅን ሙሉ ለሙሉ ማስቆም ባይቻልም መንግሥት ትልቁን ድርሻ መውሰድ እንደሚገባው መምህር እስጢፋኖስ አመልክተዋል፡፡ ሕጎችን በማውጣት ፖሊሲዎችን በማውጣት ጫናውን መቀነስ እንደሚቻልም ነው ያስገነዘቡት፡፡

የሀገር ውስጥ አምራቾች የሚበረታቱበት ሁኔታ መፈጠሩ ብቻውን ውጤታማ እንደማያደርገው ጠቅሰው፤ የልባሽ ጨርቆች ንግድ ገደብ ካልተበጀለት ውጤታማ መሆን እንደማይቻል አስታውቀዋል፡፡

«የሀገር ውስጥ አምራቾች ተወዳዳሪ ሆነው መዝለቅ እንዲችሉ የታክስ እፎይታ መስጠት ይገባዋል» የሚሉት መምህር እስጢፋኖስ፤ መንግሥት በብዛት ለማምረት ችግር በሚፈጥሩ አሰራሮች ላይ ከባለሙያዎች ጋር ተቀራርቦ በመስራት ችግሩን ማቃለል እንደሚጠበቅበትም ይገልፃሉ፡፡ የዘርፉ አሰራር በየጊዜው እንደሚቀያየር ጠቅሰው፤ አምራቾችም ተወዳዳሪ ሆነው ለመቆየት ራሳቸውን የማብቃት ሀላፊነት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ‹‹ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም!››

**ዋለልኝ አየለ**

ሰሞኑን ከትምህርት ማስረጃዎች ጋር በተያያዘ ምክንያት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና እና ትራንስክሪፕት አስፈልጎኝ የቆዩ ሰነዶቼን እያገላበጥኩ ነበር፡፡ በዚያው እግረ መንገድ የሁለተኛ ደረጃ እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሰነዶቼን እያየሁ ነበር። በትዝታ ወደ ኋላ ብዙ ሄድኩ፡፡ የትዝታ ጥሩ ነገሩ ግን በትዝታው መመሰጥ ብቻ ሳይሆን በሆነ ወቅት ላይ ምን ይደረግ እንደነበር ማሳየቱ ነው፡፡

በተለይም በአንደኛ ደረጃ የትምህርት ማስረጃዎቼ ብዙ ነገር አየሁ፡፡ በግሌ ከትንሽ ወረቀት ጀምሮ መረጃዎችን የማስቀመጥ ልማድ አለኝ፡፡ ይህ የጠቀመኝ ነገር «ያኔ እንዲህ ነበር?» እያልኩ እንደ ታሪክ መጥቀሙ ነው፡፡ እንደ ስነ ዜጋና ስነ ምግባር (ሲቪክስ) አይነት ትምህርቶች ላይ ወቅታዊ ጉዳዮችን እንጠየቅ ነበር። ለምሳሌ «የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማን ይባላል?» የሚለው ጥያቄ ላይ «ስዩም መስፍን ብዬ መልሼ» ያገኘሁትን «ራይት» እንደ አዲስ ነው የኮራሁበት። ለአንድ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ የሀገሩን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማወቅ ብርቅ ሆኖ ሳይሆን ቢያንስ ግን በዚያን ጊዜ «እንዲህ እንጠየቅ ነበር?» የሚለውን የፈተና ሁኔታ እንድገመግም አድርጎኛል፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታዎች ከዓመታት በፊት የነበሩ የሥርዓተ ትምህርት ሁኔታዎችን፣ የትምህርትና የፈተና አሰጣጥ ሁኔታዎችን፣ የወቅቱን አጀንዳዎች እናይበታለን ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የመማሪያ መጻሕፍቱ ተቀምጠው ቢሆን ኖሮ የበለጠ ጥሩ ነበር ማለት ነው፡፡

ዋናው የትዝብቴ ጉዳይ ግን እነዚህ ሰነዶች በወረቀት ስለሆኑ ነው ያገኘኋቸውና በዲጂታል ቢሆን ምን ይሆን ነበር? የሚለው ነው፡፡

የብዙዎቻችሁ መልስ የሚሆነው ዲጂታል ከወረቀት በላይ ቀልጣፋና አስተማማኝ መሆኑን ነው፡ ፡ ለረጅም ዘመን የመቆየት ዕድል ያለው፣ ለአያያዝም ሆነ ከአንድ አማራጭ ወደ ሌላ አማራጭ ለማስተላለፍ ምቹ መሆኑን ነው፡፡ ከወረቀት አንፃር ሲታይ፤ ወረቀት ኋላቀር፣ ዲጂታል ደግሞ ዘመናዊ ናቸው፡፡

አሁን ግን ሳስበው «ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም» የተባለው ለአበው ዘመን ብቻ አይደለም፤ ለዚህኛው ለዲጂታሉ ዘመንም የሚሆን ይመስለኛል። ምክንያቱም ከዲጂታል መረጃዎቼ በላይ የወረቀት መረጃዎቼን በብዛት ስላገኘኋቸው ነው፡፡

የእጅ ስልኬ ላይ ብዙ መረጃዎችን አስቀምጣለሁ። በማህበራዊ የመገናኛ ዘዴዎች ብዙ ነገሮችን አያለሁ። በማይበት ጊዜ የሚያስቁ ነገሮች ሳገኝ፣ ታሪካዊነት ያላቸው መረጃዎች ሳገኝ፣ የሆነ ጊዜ ላይ ያስፈልጉኛል ብዬ የማስባቸውን ማብራሪያዎች ሳገኝ «ሴቭ» አደርጋለሁ፡፡ በተንቀሳቀስኩባቸው አጋጣሚዎች አስገራሚ ነገሮችን ሳስተውል፣ የሚያምር ተፈጥሮ ሳገኝ ፎቶ አነሳለሁ፡፡ በአጠቃላይ በእጅ ስልኬ ላይ ዘመናዊ በሆነ መንገድ ብዙ መረጃዎችን አስቀምጣለሁ፡፡

ችግሩ ታዲያ የሆነ ወቅት በሆነ አጋጣሚ አንዳንዶቹን አጠፋቸዋለሁ፡፡ ለምሳሌ የሆነ ፋይል ስፈልግ «ስክሮል» እያደረኩ ቶሎ ላላገኘው እችላለሁ። በዚህን ጊዜ «የማያስፈልገውን ሁሉ ሰብስቤ ሰብስቤ ነው የሚያስቸግረኝ» የሚል ሀሳብ ይመጣብኝና አያስፈልጉም ያልኳቸውን አጠፋቸዋለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እየነካካሁ ባለሁበት «ለምን ቦታ ይይዛል?» በሚል አሁንም አያስፈልጉም ያልኳቸውን አጠፋቸዋለሁ፡፡ ግን የሆነ ጊዜ ላይ ያስፈልጉኛል፡፡

ከወረቀቶቹ ጋር ግን ዕለት በዕለት አልገናኝም። ቦታቸውን ይዘው ይቀመጣሉ፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ ቢያስፈልገኝ ነው፡፡ ያኔ ደግሞ እንደ ትዝታ ጭምር ይሆኑብኛና በስስት ነው የማያቸው፡፡

ይህንን ስል ግን ወረቀትን ከዲጂታል እያስበለጥኩ አይደለም፡፡ መረጃ አያያዝ እንደ ብልህነታችንና ጉብዝናችን ነው የሚወሰነው፡፡ በወረቀትም ቢሆን ፋይል ስናገላብጥ፣ ወረቀት ሲከመርብን «የማያስፈልገውን ሁሉ ሰብስቤ ሰብስቤ» የሚል ሀሳብ ይመጣብንና እየመረጥን መጣል እንጀምራለን። የተጣለው ወረቀት የእሳት እራት ይሆንና ጭራሹንም አመድ ሆኖ ይቀራል፡፡ ሲቀጥል ለአደጋ የመጋለጥ ዕድሉም ሰፊ ነው፤ በቀላሉ ለውሃ እና ለእሳት ተጋላጭ ነው፡፡ ሰፊ ቦታ የመያዝ ዕድሉም የሚታወቅ ነው። የዲጂታል መረጃዎች የእጅ ስልክ ላይ ወይም «ላፕቶፕ» ላይ በዝተው ቢያስቸግሩን በ«ሀርድ ዲስክ» አድርጎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ዘመናዊነቱና ቀልጣፋነቱም ይሄው ነው፡፡

ዋናው ጉዳይ ግን ዲጂታል ይሻላል ወይስ ወረቀት? የሚል ክርክር አይደለም፡፡ በሁለቱም በኩል 100% አስተማማኝ አለመሆኑ ነው፡፡ አስተማማኝነቱ ቢያንስ 90 ቢበዛ 99 በመቶ ቢሆን ነው፡፡ ልብ ብላችሁ ከሆነ ባለፈው ዓመት «ጉግል» አንድ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ነበር፡፡ ይሄውም የቆዩ እና እየተንቀሳቀሱ ያልሆኑ አካውንቶች ላይ ያሉ የኢሜል መረጃዎች ሊጠፉ ስለሚችሉ ጥንቃቄ አድርጉ የሚል ነበር፡፡ በአጋጣሚ ሳይጠቀምበት የቆየ ሰው ያጠራቀማቸው መረጃዎች ሁሉ ይጠፋሉ ማለት ነው፡፡

አሁንም ባለፈው ዓመት የሜታ ካምፓኒ ፌስቡክ ላይ ችግር ተፈጥሮ ስለነበር እንደዚሁ ይቅርታ ጠይቋል። ስለዚህ የበይነ መረቡ ዓለምም ችግር ሊያጋጥመው ይችላል ማለት ነው፡፡ ልክ በሰዎች ሕይወት ላይ እንደ ኮቪድ-19 አይነት ወረርሽኝ እንደሚከሰተው ሁሉ ሰው ሰራሽ የሆነው የበይነ መረቡ ዓለም ላይ ችግር አይፈጠርም ማለት አይቻልም፡፡

አንዳንድ ወገኖች በአጉል ሰለጠንን አይነት እሳቤ «በዚህ ዘመን ወረቀት?» እያሉ ይገረማሉ፡፡ ወረቀት እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ባለ ገና ብዙ በሚቀረው ሀገር የዲጂታሉን ዓለም በፈጠሩት ሀገራትም አልቀረም፡፡ የትልልቅ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ዜና አንባቢዎች ዛሬም እስኪርቢቶ ይዘው ይታያሉ፡፡ ምናልባት የእስኪርቢቶ ዘመን ትውስታ ስላልወጣላቸው ይሆን?

በነገራችን ላይ የአሁኑ የቴሌግራም ዘመን ትውልድ ቀደም ባለው ዘመን ቴሌግራም የሚባል የመልዕክት መላላኪያ መኖሩን አያውቅ ይሆናል እኮ! በድሮው ጊዜ (ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ) ሰዎች መልዕክት የሚለዋወጡት በቴሌግራም ነበር፡፡ ይህ የድሮው ቴሌግራም ኤሌክትሪካል በሆነ መንገድ የምሥጢር ቁጥር ምልክት በመጠቀም የሚለዋወጡበት ነበር፡፡ እነሆ ከ170 ዓመታት በኋላ በአውሮፓውያኑ 2013 ደግሞ አሁን የምንጠቀምበት ዘመናዊው ቴሌግራም ተጀመረ ማለት ነው፡፡

ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ የድሮ የሆኑ ነገሮች፤ መነሻ ናቸውና ለማስታወስ ዘመናዊ ነገሮች በስማቸው ይሰየሙላቸዋል፡፡ እግረ መንገዳቸውንም ውለታቸውን ያስታውሳሉ፡፡ በሌላ በኩል አሰራሩ ፈጣን እና ምቹ ይሁን እንጂ የሚሰጡት አገልግሎትም ይመሳሰላል። በድሮው ጊዜ የነበረው ቴሌግራም መልዕክት መለዋወጫ ነበር፤ የአሁኑ ቴሌግራምም መልዕክት መለዋወጫ ነው፡፡ ጥራትና መጠኑ እየሰፋ ይሄዳል፡፡

«ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም» ይባላልና ወረቀትን ጊዜ ያለፈበት ኋላቀር አሰራር አድርጎ ማየት ስህተት ነው፡፡ ለአገልግሎት ምቹነት ድሮ በወረቀት የነበሩ ነገሮችን ወደ ዲጂታላይዝድ አገልግሎት ሲለወጡ ወረቀቱ ባይጣል ጥሩ ነው፡፡ ለእነዚያ ወረቀቶች የሚሆን ቦታ አይጠፋም፡፡ የኢንተርኔቱ ዓለም ችግር ቢያጋጥመው እንኳን እነዚያ ወረቀቶች ምስክር ይሆናሉ፡፡

በአጠቃላይ፤ ብዙ መሥሪያ ቤቶች የዲጂታል አገልግሎት በሚል ስም ወረቀቶችን አውጥተው እየጣሉ ነውና ይህ ነገር ቢታሰብበት!

## ነፃ ሃሳብ

# ለወደብ ጥያቄያችን ትክክለኛ አረዳድ ለመፍጠር!

**ታሪኩ ዘለቀ**

የታሪክ ድርሳናት እንደሚያሳዩት፤ ከ1983 ዓ.ም በፊት ኢትዮጵያ የባህር በር የነበራት ሀገር ናት። ይሁን እንጂ በጊዜ ሂደት ፖለቲካዊ ምክንያቶች በወለዷቸው ውስብስብ ችግሮች የወደብ ባለቤትነቷን ተነጥቃ የሌሎች ሀገራትን ወደቦች ተጠቃሚ ለመሆን ተገዳለች፡፡ በዚህም የኢኮኖሚ እድገቷ ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል። በዚህም ሀገሪቱ ለወደብ አገልግሎት ከ300 እስከ 500 መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወጪ ለማድረግ እየተገደደች ነው ፡፡

ወደብ አልባነት የአንድ ሀገር ልማትና እድገት እንቅፋት ነው፡፡ የባህር በር ያለው ሀገር ከሌለው፣ ዓመታዊ እድገቱ ላይ ቢያንስ 25 በመቶ ተጨማሪ እድገት እንደሚኖረው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ ማለት አንድ ሀገር 10 በመቶ ዓመታዊ እድገት ቢያስመዘግብ የባህር በር ያለው ከሆነ የባህር በር ከሌለው ከ3 ከመቶ በላይ ተጨማሪ እድገት ይኖረዋል፡፡

ሀገራችን ከ120 ሚሊዮን የሚበልጥ ህዝብ ይዛ የባህር በር ባለቤት አለመሆኗ ከኢኮኖሚያዊ ተጎጅነቷ ባለፈ ለቀጣናው ሰላምና ደህንነት፤ ፖለቲካዊ አንድምታ ትልቅ አቅም ሊፈጥርለት እንደሚችል ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ይህም በራሱ ካላት ጂኦ - ፖለቲካዊ አቀማመጥ አንጻር ብሄራዊ ጥቅሞቿዋን በተሻለ መንገድ ለማስጠበቅ ይረዳት እንደነበር ይናገራሉ።

ትናንት አክሱምን ፈልፍላ ሮሃን ያነፀች ሀገር፤ መርከብ አበጅታ ቀይ ባህርን የቀዘፈች ዛሬ የባህር በር ከሌላቸው 17 የአፍሪካ ሀገራት አንዷ ለመሆን ተገዳለች፡፡ አንዳች መፍትሄ ካላገኘች በቀጣይ አስርት ዓመታት የህዝብ ብዛቷ 150 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ የምትገመተው ኢትዮጵያ ይህን ያህል ህዝብ ካላቸው የዓለም ሀገራት ብቸኛዋ ወደብ አልባ ሀገር ሆና መቀጠሏዋ የማይቀር ነው።

በርግጥ ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፍ ሕግና ከታሪክና ከሞራል አንጻር የባህር በር የማግኘት መብት አላት ። ይህ መብቷ በሰላማዊ መንገድ አካባቢው ካሉ የወደብ ባለቤት ከሆኑ ሀገራት ጋር የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ባደረገ መንገድ ተጨባጭ ለማድረግ የጀመረችው የእንነጋገር ጥሪት በብዙዎች ዘንድ ይበል የሚባል ሆኖ ተገኝቷል። የአካባቢው ሀገራትን በማስተሳሰር ኢኮኖሚያዊ ውህደትን ለማፋጠንም በራሱ አንድ አቅም እንደሚሆን እየተነገረም ነው።

ይህንን የአካባቢው ሀገራትና ህዝቦችን የጋራ ተጠቃሚነት መሰረት ያደረገ የእንነጋገር ጥሪ በማጣመም እና ጉዳዩን ባልተገባ መንገድ በመተርጎም በሀገራት መካከል አለመተማመን እንዲሰፍን የሚንቀሳቀሱ ሀይላት አሁንም እውነታውን ባልተገባ መንገድ /በአፍራሽ መንገድ በእጃቸው ባሉ በመገናኛ ብዙኃኖች ማራገባቸውን እንደቀጠሉ ነው፡፡

እነህ አካላት በቀጣናው ለሚገኙ ህዝቦች ብሩህ ነገዎች በጎ እይታ የሌላቸው መሆናቸውን በተደጋጋሚ በሚሰሩት ዘገባዎቻቸው አስመስክረዋል፡፡ የኢትዮጵያን የባህር በር ይገባኛል ጥያቄ ማንሳት ጦርነት ፍለጋ አድርገው በማናፈስ፣ ከአውዱ ውጪ የሆነ የተሳሳተ መረጃ በማሰራጨት፤ ለሀገሪቱ እድገት በጎ አስተሳሰብ የሌላቸው አካላት /ሀገራት ጭምር ሴራ አስፈፃሚዎች በመሆን እየተንቀሳቀሱ ነው ፡፡

ኢትዮጵያ ጦሯን ለጦርነት እያሰናዳች ነው፣ በሀገሪቱ ያልተገባ ጉዳይ ጎረቤት ሀገራት ቁጣቸውን እየገለጡ ነው ..ወዘተ የሚሉና ሌሎች የተዛቡ መረጃዎችን በመልቀቅ የቀጣናውን ሀገራት ሰላም ለማናጋት ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የጀመረችው ልማት ለጎረቤት ሀገራት ይዞት የመጣውን ትሩፋት ዓይናቸውን ገልጠው እንዲያዩ የጽልመት መጋረጃዎችን በመስፋት ላይ ናቸው።

የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት እጣ ፈንታቸውን በጋራ ሊወስኑ የሚችሉባቸውን እድሎችን፤ባልተገባ መንገድ በመተርጎም ሀገራቱ ከነበሩባቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች ወጥተው ለህዝቦቻቸው ዘላቂ እና ሁለንተናዊ እድገት ሊሰሩ የሚችሉባቸውን አጋጣሚዎች የአደጋ ምንጭ አድርጎ በማቅረብ በመካከላቸው አለመተማመን እንዲሰፍን እንቅልፍ እንዳጡ ነው፡፡

የኢትዮጵያ በባህር ጥያቄዋ ዙሪያ እንነጋገር የሚለው ሀሳቧ በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሰረተና የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን የንግድ ትብብር የሚያጠናክር ነው፡፡ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት ላይ ያተኮረ ፣ለቀጣናው ህዝቦች ብሩህ ነገዎች ተስፋ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ይህን ግልጽ የሆነ እውነታ የጦርነት ነጋሪት ጉሰማ አስመስሎ ማቅረብ ከጀርባው ሌላ የሴራ ጥንስስ ለመኖሩ አመላካች ነው፡፡

በጉዳዩ ዙሪያ ጦርነትን የሚያራግቡ ዘገባዎች ተሰራጭተው መመልከት የሆነ አካል ቀጣናውን ወደ አለመረጋጋት እንዲያመራ ቀን ከሌሊት እየሰራ እንደሆነ ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንም። በተለይም በኢትዮጵያ እየተስተዋለ ያለውን ለውጥና ለውጡ እያመጣ ያለው ስኬት ያሳሰባቸው ኃይሎች ሴራ አካል እንደሚሆን ለመገመት የሚከብድ አይሆንም።

የወደብ /የባህር በር ጉዳይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት የህልውና ጉዳይ እየሆነ እንደሚሄድ ለማንም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በአግባቡ መገንዘብ ለሚችል ባለ አእምሮ የተሰወረ አይደለም። ጉዳዩ በዚህ ሰዓት መነሳቱም ፀብ አጫሪ የሚያሰኝ አይደለም፡፡ መንግሥትም የጉዳዩን አሳሳቢነት ለአካባቢው ሀገራት ወንድም ህዝቦች ለማሳየት መሞከሩ ጠብ አጫሪ የሚያሰኘው አይደለም። ይህን ማድረግ እንደ መንግሥት የሚጠበቅበት ነው።

ጉዳዩን ሲያነሳው በጉልበት/በኃይል እፈጽመዋለሁ አላለም፡፡ ለጦርነት ነጋሪት አስጎሽሞ ተነስ፣ ታጠቅ አላለም። እንነጋገር፣ በሰጥቶ መቀበል መርህ የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ባደረገ መንገድ ጉዳዩን እንመልከተው ነው ያለው፡፡ ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከሰቱ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበት መንገድ ነው። ሊበረታታ እና እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

የኢትዮጵያን የባህር በር መሻት "ቀጣናውን ወደ ጦርነት የሚወስድ ነው" የሚሉ ዘገባዎች በሰላም እና በመግባባት የተፈታውን የኢትዮጵያና የጎረቤት ሀገራት ግንኙነት ወደአልተፈለገ አቅጣጫ ለመውሰድ መፈለጋቸውን ሁነኛ አመላካች ነው። ይሁን እንጂ ጉዳዩን ከምጣኔ ሀብታዊ ትስስር ጋር ብንመለከተው የምሥራቅ አፍሪካ ማቅ ሳይሆን ወርቅ የሚያለብስ ስለመሆኑ ቅንጣት ያህል አጠራጣሪ አይደለም፡፡

እንዳለመታደል ሆኖ አንዳንዶች የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ እድገት በበጎ እየተመለከቱት አይደለም። አስርና ሃያ ዓመታትን ተሻግረው የኢትዮጵያን ምጣኔ ሀብት እድገትን ከቀጣናው ጋር አስተሳስረው ለመመልከት ፍቃደኛም አይደሉም። እርግጥ ነው በአካባቢው ሀገራት ትናንት ላይ የነበሩ የታሪክ ስብራቶች አሁን ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የትብብር ሃሳቦች ላይ የራሳቸው የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ ፡፡ ይህ ግን በራሱ አሁን ላይ /ዛሬ ላይ የሚቀርቡ የትብብር ጥያቄዎችን ሊያዳፍኑ አይችሉም፡፡

> **ይህ የሕግ ድንጋጌ ሀገሪቱ እያቀረበች ያለውን ጥያቄ ሕጋዊ መሰረት የሚያሳብስ ነው። በዓለም አቀፍ መድረክ ሳይቀር ይሁንታ እንዲያገኝ የሚያስችለው ነው**

የህዝብ ቁጥሯ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ የምትገኘው ኢትዮጵያ የገቢ እና ወጪ ንግዷን በማሳለጥ የጀመረችውን ድህነትን ታሪክ የማድረግ የታሪክ ጉዞ ስኬታማ ለማድረግ የባህር በር ጉዳይ ወሳኝ ነው። ለዚህም በጉዳዩ ላይ ለመነጋገር ያነሳችው ጥያቄ ወቅቱን የጠበቀና ተገቢ ነው። የመንግሥት የፖለቲካ ጥያቄ ሳይሆን የመላ ህዝቦቿም የህልውና ጥያቄ ነው።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባህር ህግ አንቀፅ 69 ንዑስ 1 እስከ 5 የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ካለው ባህር የተፈጥሮ ሀብት እኩል የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ይህ የህግ ድንጋጌ ሀገሪቱ እያቀረበች ያለውን ጥያቄ ህጋዊ መሰረት የሚያላብስ ነው። በዓለም አቀፍ መድረክ ሳይቀር ይሁንታ እንዲያገኝ የሚያስችለው ነው።

ይህንን ከህግ፣ ከታሪክና ከሞራል አኳያ ተገቢ የሆነን የሀገር ጥያቄ፣ የመንግሥት የጦርነት መሻት ማሳያ አድርገው በማቅረብ የተጠመዱ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን ሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች ከመንግሥት ጋር ባለመግባባት ውስጥ ያሉ አካላት ዘገባዎቻቸው የቱን ያህል ሚዛን የሳቱና የኢትዮጵያን ህዝብና መንግሥት ፍላጎት የማይወክሉ ስለመሆናቸው ቆመው በአግባቡ ሊያስቡ ይገባል ።

ይህን መሰል የሀገራችንንና ህዝባችን ፍላጎት የሚያዛባ ትርክት፣ የኢትዮጵያን ህዝብና መንግሥት የማይወክል፤ ከዛ ይልቅ ፍላጎታቸውን በማዛባት፣ ያልተገባ ትርጓሜ እንዲያገኝ የሚያደርግ የጥፋት መንገድ ነው። ይህን ለመከላከል በተለይም የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙኃን በስፋት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። ትክክለኛውን እውነታ በተለያዩ ቋንቋዎች በማሰራጨት ዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ተገቢና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኝ መስራት፤ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነትም መፍጠር ይኖርባቸዋል።

መንግሥትም ቢሆን አሁን እያደረገ ያለው እንዳለ ሆኖ ያሉ የዲፕሎማሲ አማራጮችን በመጠቀም እውነታው ትክክለኛ መልኩን/ ቀለሙን ይዞ እንዲሄድ ማድረግ፤በጉዳዩ ዙሪያ ያሉ ዓለም አቀፍ አረዳዶች የተዛቡ እንዳይሆኑ በስፋት ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡ እያንዳንዱ ዜጋም በተለይም በውጪ ያለው የዲያስፖራ ማህበረሰብ ራሱን ከተዛቡ መረጃዎች በማቀብ እና የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት ለሀገሩና ለመላው ህዝብ ተጠቃሚነት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለሀገሩ ዘብ መሆን ይጠበቅበታል።

ከዚህም ባለፈ በጉዳዩ ዙሪያ የሚደረጉ ዲፕሎማሲያዊ ውይይቶች ግልፅና መግባባት ላይ የሚደረስባቸው እንዲሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሰፊ ሥራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። ምሁራን እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በጉዳዩ ዙሪያ ጥናቶችንና የፓናል ውይይቶችን በማዘጋጀት ጉዳዩ የበለጠ ግልጽ እንዲሆን በስፋት መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። እነዚህን ማድረግ ከቻልን በእርግጠኝነት ጉዳዩን ከጥፋት አሉባልታ መታደግ እንችላለን።

አዲስ ዘመን | ሰኞ ታኅሣሥ 22 ቀን 2016 ዓ.ም

# ዓለም አቀፍ

# የፈረንሳይዋ የመዘንጋት ችግር ያለባቸው ሰዎች መንደር

በጋዜጣው ሪፖርተር

ፈረንሳይ አንዲት መንደር አቋቁማለች- የመዘንጋት ችግር ያለባቸው ነዋሪዎች ብቻ የሚኖሩባት። ላንዳይስ አልዛይመር ትሰኛለች።

በዚህች በደቡብ ምዕራብ ፈረንሳይ በምትገኘው መንደር የሚኖሩ ነዋሪዎች ሁሉም የመዘንጋት ችግር አልዛይመር የተሰኘው ህመም አለባቸው።

ወደ መገበያያ መደብር እና ሬስቶራንት ከመሄድ በተጨማሪ የመንደሯ ነዋሪዎች ቲያትር ቤት ሄደው ቲያትሮችን እንዲመለከቱም ይበረታታሉ።

የተለያዩ ቡድኖችንም በመቀላቀል ህይወታቸውን ማስቀጠል እንደሚችሉም ይነገራቸዋል።

ቢቢሲ በዚህች መንደር ያገኛቸው ባለትዳሮቹ ፊሊፕ እና ቪቪያን የመርሳት ችግር እንዳለባቸው በምርመራ ቢረጋገጥም የተለመደውን ህይወታቸውን ለማስቀጠል እየሞከሩ ይገኛሉ።

“በእግራችን ረጅም መንገድ እንሄዳለን፣ እንራመዳለን” ይላሉ ፊሊፕ መንገዳቸውን እየተመለከቱ።

ቢቢሲም ደስተኛ ናችሁ? የሚል ጥያቄ ሲጠይቃቸውም እሳቸውም ፊታቸው ወዲያውኑ ራሳቸውን አዙረው ደመቅ ባለ ፈገግታ “አዎ በእውነት! ደስተኛ ነን” አሉ በማያጠራጥር ድምጸት።

የጊዜ ዑደት በዚህች መንደር የተለየ ነው ይላል የቢቢሲ መንደር አስጎብኚ።

እንደሌላው የከተሜ ኑሮ ቀኑ ለተለያዩ ጉዳዮች አልተከፋፈለም።

ለቀጠሮ፣ ገበያ ለመውጣት ወይም ምግብ ለማብሰል እና ለማጽዳት የተቀመጡ ሰዓቶች የሉም።

በተቻለ መጠን የመንደሯ ነዋሪዎች ህይወትን በተረጋጋ እና ነጻነት በተሞላበት መንገድ እንዲኖሩ ለማድረግም ነው የሚሞከረው።



የመንደሯ ሁኔታ በቅርበት ክትትል የሚደረግበት ሲሆን፣ ፕሮፌሰር ሄሌኔ አሚዬቫ እንደሚሉት በበሽታው ሂደትም ላይ ለየት ያለ ተጽእኖ እያመጣ እንደሆነም የእስካሁኑ ውጤቶች ያሳያሉ።

“የመዘንጋት ችግር ያለባቸው ሰዎች ወደ ህክምና ተቋማት ወይም ማዕከላት ሲገቡ የምናየው ጉዳይ በተፋጠነ ሁኔታ የግንዛቤ ሁኔታቸው ያሽቆለቁላል። በዚህች መንደር ውስጥ ግን ይህንን አልተመለከትንም” ይላሉ።

“የበሽታው ሂደት ቀስ ባለ ሁኔታ እንደሚሄድ ተገንዝበናል” ሲሉም ያስረዳሉ።

“እንደነዚህ አይነት መንደር ማቋቋም በክሊኒክ በሚደረጉ የህክምና ውጤቶች አቅጣጫ ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉም ለማመን ምክንያቶች አሉን” ብለዋል።

በተጨማሪም የመርሳት ችግር ያለባቸው ቤተሰቦቻቸው እንክብካቤ ከፍተኛ የጥፋተኝነት ስሜት እና ጭንቀት ላይ የጣላቸውም ቤተሰቦች እንዲህ አይነት መንደር እፎይታ ሰጥቷቸዋል።

የ89 ዓመት ዕድሜ ያላቸው እና የመርሳት ችግር ያለባቸውን እናቷን ልትጎበኝ የመጣችው ዶሚኒክ “የአዕምሮ ሰላሜን አግኝቻለሁ። ምክንያቱም ደህንነቷ ተጠብቆ አዕምሮዋም ሰላም የሚሆንበት ስፍራ ላይ እየኖረች ስለሆነ ነው” ትላለች።

የእናቷ መኝታ ክፍልም ግድግዳ ላይ የቤተሰብ ፎቶዎች እና ስዕሎች ተሰቅለዋል። በተጨማሪም ከዚህ ቀደም እናቲቱ ሲጠቀሙበት በነበሩ የቤተሰብ እቃዎች ተሞልቷል። በመስኮቱም በኩል የአትክልት ስፍራው ተንጣልሏል።

እሳቸውን ለመጎብኘት የተቀመጠ ሰዓት የለም። ሰዎች በፈለጉበት ሰዓት መጥተው ይጎበኟቸዋል። ሲፈልጉም ይሄዳሉ። ዶሚኒክ እና እህቶቿ እናታቸው እንዲህ አይነት እጅግ በጣም ጥሩ እንክብካቤ ይገጥማቸዋል ብለው ፍጹም እንዳልጠበቁ ታስረዳለች።

“ትቼያት ስሄድ እፎይታ ይሰማኛል። ስመጣም ልክ የቀድሞ ቤት እንደምጎበኛት ነው የሚሰማኝ። ከእናቴ ጋር በቤታችን ነን” ስትልም ስለ መንደሯ ትናገራለች።

መንደሯ በቪላ ቤቶች የተከፋፈለ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ቪላም ወደ ስምንት የሚጠጉ ነዋሪዎች አሉ። በቪላውም ውስጥ የሚኖሩት ነዋሪዎች የጋራ ማዕድ ቤት፣ ሳሎን እና የመመገቢያ ክፍሎችንም ይጋራሉ።

በመንደሪቷ 120 የሚጠጉ ነዋሪዎች ሲኖሩ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው የእንክብካቤ ሰጪ ባለሙያዎች አሉ። የበጎ ፈቃደኞች ቁጥር ከነዋሪዎቹም ሆነ ከባለሙያዎች ይበልጣል።

የመዘንጋት (የመርሳት ችግር) ጭካኔው እየከፋ መሄዱ እና መድኃኒት አለመኖሩ ነው። ነገር ግን በዚህች መንደር ያሉ ነዋሪዎች ህመማቸው እየከፋ ሲሄድ የሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ይሰጣቸዋል።

የመንደሩ ነዋሪዎች የተወሰነ መዋጮ ቢያወጡም አጠቃላይ ወጪውም በክልሉ የፈረንሳይ መንግሥት ነው የሚሸፈነው። መንደሪቷንም ለማቋቋም መንግሥት 22 ሚሊዮን ዶላር አውጥቶበታል።

መንደሯ በአውሮፓውያኑ 2020 ስትቋቋም በዓይነቷ ሁለተኛዋ ስትሆን ብቸኛዋም የምርምር ፕሮጀክት አካል ናት።

በዓለም ላይ እንደዚህች ያሉ የአዕምሮ መዘንጋት ችግር ላለባቸው የተቋቋሙ መንደሮች ቁጥር ከአስራ ሁለት ያነሱ እንደሆኑ ይታሰባል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንዘብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን

# ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዱባይ ማራቶን ስድል ይጠበቃሉ

ቦጋለ አበበ

በመካከለኛው ምሥራቅ ከሚካሄዱ ታላላቅ የጎዳና ላይ ውድድሮች አንዱና ዋነኛው የዱባይ ማራቶን ነው፡፡ የዱባይ ማራቶን ከፍተኛ የገንዘብ ሽልማት የሚገኝበት ከመሆኑ በዘለለ የኢትዮጵያውያን አትሌቶች ፍፁም የበላይነት የሚንፀባረቅበት መሆኑ ይታወቃል፡፡

የፈረንጆቹ አዲስ ዓመት የመጀመሪያው ትልቅ የጎዳና ላይ ውድድር የሆነው የዱባይ ማራቶን የ2024 መርሀ ግብሩን በመጪው ዓርብ ሲያከናውንም የተለመደው የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የበላይነት ይጠበቃል። ለዚህም በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከወዲሁ መዘጋጀታቸው ታውቋል፡፡

የ2023 የዱባይ ማራቶን በአንድ ለየት ያለ ክስተት ይታወሳል፡፡ ይህም በሁለቱም ፆታ አንድ ቤተሰብ ቻምፒዮን የሆነበት ታሪክ ነው፡፡ የ2022 የዓለም የማራቶን ቻምፒዮኑ ኢትዮጵያዊ አትሌት ታምራት ቶላ ባለቤት የሆነችው አትሌት ዴራ ዲዳ በሴቶች አሸናፊ ስትሆን የታምራት ወንድም አብዲሳ ቶላ ደግሞ በወንዶቹ ፉክክር አሸናፊ ነበር፡፡ ታምራት ቶላም ቢሆን ከዓመታት በፊት ይህንኑ የዱባይ ማራቶን ያሸነፈ አትሌት በመሆኑ በውድድሩ ስኬታማ ቤተሰብ አሰኝቷቸዋል፡፡

የአምናዋ ቻምፒዮን ዴራ ዲዳ 2018 እና 2020 ላይ በዚሁ ውድድር ሰባተኛና አምስተኛ ደረጃን ይዛ ያጠናቀቀች ሲሆን፤ ባለፈው ዓመት ግን ፉክክሩ ገና ሁለት ኪሎ ሜትሮች ሲቀሩት ቀድማ በመውጣት በአስደናቂ ብቃት 2፡21፡11 በሆነ ሰዓት ማሸነፏ ይታወሳል፡፡ ይህች አትሌት ዘንድሮም በውድድሩ አሸናፊነትን ለማስጠበቅ መዘጋጀቷ ታውቋል፡፡ የባለቤቴ ወንድምና የአምናው ቻምፒዮን አብዲሳ ቶላ ግን በጉዳት ምክንያት በዘንድሮው ውድድር እንደማይፎካከር ታውቋል፡፡

ፈጣን ሰዓት ከሚመዘገብባቸው የማራቶን ውድድሮች አንዱ በሆነው የዱባይ ማራቶን ዘንድሮ ዴራ ዲዳን ጨምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለ2024 የፓሪስ ኦሊምፒክ ሀገራቸውን ወክለው በታላቁ መድረክ ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ሰዓት ለማስመዝገብ ጠንካራ ፉክክር እንደሚያደርጉ ይጠበቃል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ አስደናቂ ለውጥና ብቃት እያሳየች የምትገኘው አትሌት ዴራ ዲዳ በ2023 በ10 ሺ ሜትር እንዲሁም በግማሽ ማራቶን ውድድሮች የራሷን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገብ ችላለች፡፡ ከዚህ ስኬት ከሰባት ወራት በኋላም ነበር የዱባይ ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ ማሸነፍ የቻለችው። የ27 ዓመቷ አትሌት ከዱባይ ማራቶን ድሏ በኋላም ዘንድሮ በበርሊን ማራቶን 2፡19፡24 የሆነ የራሷን የማራቶን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገቧ ይታወሳል፡፡ በአሁኑ የዱባይ ማራቶንም እያሳየች የምትገኘውን ለውጥ ታስቀጥላለች ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በ10 እና 5ሺ ሜትሮች የሁለት ጊዜ የኢትዮጵያ ቻምፒዮና ድራ ዲዳ «ባለፈው የዱባይ ማራቶን ውድድሩን መምራት ስትጀምር እንደማሸንፍ አውቅ ነበር፣ ፉክክሩም አስደናቂ ነው፣ ከእኔ ቀጥሎ የወንዶቹን ውድድር አብዲሳ ማሸነፉ ደግሞ የተለየ ስሜት ነበረው» በማለት ስለ አምናው ውድድር ታስታውሳለች።

የሁለት ጊዜ የዓለም አገር አቋራጭ ቻምፒዮና የብር ሜዳሊያ አሸናፊዋ ዴራ ዘንድሮም ዱባይ ላይ ሌላ ታሪክ እንደምትሰራ የውድድሩ አዘጋጆች ተስፋ አድርገዋል፡፡

የዱባይ ማራቶን ውድድር ዳይሬክተር ፒተር ኮኔርቶን « ሁሌም ቢሆን የውድድሩ አሸናፊዎች ዳግም ሲወዳደሩ ያስደስተናል፣ ከአንድ ቤተሰብ ሁለት ሰው ሲያሸንፍ ማየት ትልቅ ስኬት ነው፣ ዘንድሮም ዴራ ቻምፒዮንነቷን ለማስጠበቅ ወደ ውድድሩ በመመለሷ ተደስተናል» በማለት ለመገናኛ ብዙኃን አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡



አትሌት ዴራ ዲዳ የአምናውን የዱባይ ማራቶን ድሏን ለመድገም ተዘጋጅታለች፤

በዘንድሮው ውድድር የዴራ ዲዳ ጠንካራ ተፎካካሪ እንደምትሆን የምትጠበቀው የሮተርዳምና የኦሳካ ማራቶን አሸናፊዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ሄቨን ሀይሉ የአሸናፊነት ፉክክሩን ከተቀላቀሉ ጠንካራ አትሌቶች አንዷ ሆናለች። የ25 ዓመቷ ድንቅ አትሌት በርቀቱ የራሷን ፈጣን ሰዓት በ2፡20፡19 ያስመዘገበችው በ2019 አምስተርዳም ማራቶን ላይ ነው። የ2023 የሮም ማራቶንን በ2፡23፡02 ያሸነፈችው ኬንያዊቷ ቤቲ ቼፕከዎኒ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ጠንካራ ፉክክር ታደርጋለች፡፡

በዘንድሮው የዱባይ ማራቶን በወንዶች እስከ ትናንት በይፋ እንደሚሳተፉ ያረጋገጡ ኢትዮጵያውያን ሁለት አትሌቶችን አዘጋጆቹ ይፋ አድርገዋል፡፡ በ2022 ሀምበርግ ማራቶን 2፡05፡07 የራሱን ፈጣን ሰዓት ያስመዘገበው አትሌት ወርቅነህ ታደሰ አንዱ ነው፡፡ ሌላኛው አትሌት ከበደ ቱሉ ሲሆን 2020 ሙምባይ ማራቶን ላይ ከተወዳደረ በኋላ በዘንድሮው የሴቪሊ ማራቶን የራሱን ምርጥ ሰዓት በ2፡05፡19 ማስመዝገብ የቻለ ነው። በዘንድሮው የዱባይ ማራቶን በሁለቱም ፆታ የሚሳተፉ ሌሎች በርካታ አትሌቶችም በመጪዎቹ ቀናት ይታወቃሉ፡፡